የክርስትና መስፋፋት በማዕከላዊ ምዕራብ አፍሪካ 1878-1914 ዓ.ም.

የምዕራፍ ሀያ ሦስት ጥናታችንን ያጠናቀቅነው፥ በናይጀሪያ የነበረውን የወንጌል ሥራ እድገት በመመልከት ነበር። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ከካሜሩን እንጀምርና ክርስትና በተለያዩ ስፍራዎች ያሳየውን እድገት ካርታ ላይ በደቡብ አቅጣጫ በመጓዝ እንመለከታለን።

ካሜሩን

በምዕራፍ ሀያ ሁለት እንደተመለከትነው ካሜሩን የጀርመን ቅኝ ግዛት የሆነችው በ1884 ዓ.ም. ነበር። በቀጠሉት ዓመታት ጀርመኖች ምድሪቱን ጠበቅ አድርገው ያዟት። የጀርመን ቅኝ ገዢዎች የወንጌል ሥራ እንዳይስፋፋ በሁለት መንገዶች እንቅፋት ሆነው ነበር። የመጀመሪያው ጀርመናዊ ያልሆነን ማንኛውንም ሚስዮናዊ መጠራጠራቸው ሲሆን፥ በዚህም ሳቢያ ከእንግሊዝ ወይም ከፈረንሳይ የሚስዮን ማኅበራት የሆኑ ሚስዮናውያን ሥራቸውን መቀጠሉ ከባድ ሆኖባቸው ነበር። ቀጥሎ ደግሞ ትምህርት ቤቶች በሙሉ ጀርመንኛን የማስተማሪያ ቋንቋቸው አድርገው እንዲጠቀሙበት ታዘዙ። በዚህም መሠረት ከአርባ ዓመታት በላይ ካሜሩን ውስጥ ሲሠሩ የቆዩት የባፕቲስት ሚስዮን ትምህርት ቤቶች የማስተማሪያ ቋንቋቸውን መለወጥ ግድ ሆነባቸው። በአንጻሩ ደግሞ የጀርመኖች ቅኝ ገዢነት ያስከተለው ጥቅም ነበር። እነሱም በተለያዩ ነገዶች መካከል የነበረው ጦርነት መቀነስ፥ መንገድና የፖስታ አገልግሎት የመሳሰሉ የመገናኛ ዘዴዎች መዘርጋት ናቸው። ይህ ምቹ ሁኔታ ሚስዮናውያኑ የክርስትናን መልእክት ይዘው ወደ ውስጥ እንዲዘልቁ ረዳቸው።

በጀርመናውያኑ ምክንያት ከሁሉም የላቀ መከራ የደረሰባት አልፍሬድ ሻከር በተባለ ሚስዮናዊ አማካይነት ዱዋላ አካባቢ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ናት። ሻከር እንግሊዛዊ ስለነበር፥ የጀርመን ቅኝ ገዢዎች የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ያለችባቸውን አካባቢዎች መግዛታቸውን አጥብቆ ይቃወም ነበር። በ1885 ዓ.ም. የባፕቲስት ሚስዮን በነበረበት አካባቢ በሁለት ነገዶች መካከል ጦርነት ይካሄድ ጀመር። ይህ ጦርነት እንዲያበቃ ጀርመኖች የኃይል እርምጃ ሲወስዱ፥ የባፕቲስት ሚስዮን ጣቢያዎችንም አብረው ደመሰሷቸው። ከዚህም የተነሣ የእንግሊዝ ባፕቲስት ሚስዮን ካሜሩን ውስጥ ሥራውን

መቀጠሉ አስቸጋሪ እንደሚሆንበት ተገነዘበ። ምክንያቱም የጀርመን መንግሥት ሚስዮኑን በጠላትነት ይቃወመው ጀመር። በዚሁ መሠረት በሚስዮኑ ጣቢያዎች የሚከናወኑ ነገሮች ሁሉ በጀርመንኛ ወይም በአገሪቱ ማለት በዱዋላ ቋንቋ እንዲሆኑ የጀርመን መንግሥት ይጠይቅ ነበር። ስለዚህ የእንግሊዝ ባፕቲስቶች እዚያ ያለውን ስፍራቸውን የጀርመን ባዘል ሚስዮናውያን እንዲረከቧቸው ጠየቁ። ታኅሳስ 23 ቀን 1886 ዓ.ም. የመጀመሪያው የባዘል ሚስዮን አዲሱን ሥራ ለመጀመር ካሜሩን ቤቴል ደረሰ።

የጀርመን ሚስዮናውያን ስፍራው ደርሰው ወዲያውኑ ሥራ ቢጀምሩም፥ ከመጀመሪያዎቹ መልክተኞች አንዳንዶቹ በወባ በሽታ ሞቱ። ከዚሁ ጋር ብዙዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት በሥነ-ምግባር ዝቅ ያሉ መሆናቸውን የባዘል ሚስዮናውያን ገና ሥራ እንደጀመሩ ተረዱ። ስለዚህ ከዓለም አምሮት የመራቅን አስፈላጊነት ለምእመናኑ ይሰብኩ ጀመር። ስብከቱ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባላትን አስቆጣና መከፋፈልን አስከተለ። በ1890 ዓ.ም. የጀርመን ባፕቲስት ሚስዮን አባላት ወደ ስፍራው በመምጣት ከባዘል ሚስዮን ተገንጥለው ከወጡት የቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር ለመሥራት ሞከሩ። ሙከራቸው በጊዜው ውጤታማ ባይሆንም፥ ሚስዮኑ ግን ቆይቶ እድገት አሳይቷል።

የባዘል ሚስዮን አባላት ከ1886-1903 በነበሩት ዓመታት ከባፕቲስቶች በተረከቧቸው ሥራዎችና ጣቢያዎች ራሳቸውን ሲያለማምዱ ቆዩ። በእነዚህ ጊዜያት የወንጌል ምስክርነት በታማኝነት ተሰራጨ። የባዘል ሚስዮናውያን ጀርመናውያን ስለነበሩ፥ ብዙ አፍሪካውያን ሚስዮናውያኑን የአዲሱ የጀርመን መንግሥት አካል አድርገው ይቆጥሯቸው ጀመር።

ዝውውሩ ከባፕቲስቶች ወደ ባዘሎች እንደተደረገ ወዲያውኑ ብዙ ሰዎች ወደ ክርስትና ተለወጡ። ለዚህ ምክንያቱ ጥቁሮቹ እምነቱን በጀርመናውያኑ ከተመሠረተው አዲስ ሥርዓት ጋር ስላያያዙት ሊሆን ይችላል። መንግሥት ወደ መሀል አገር የሚያስገቡ መንገዶች በሠራ ቁጥር፥ የባዘል ሚስዮንም ሥራውን አስፋፋ። በርካታ ነገዶች ክርስትናን ፈልገው ሳይሆን፥ እራሳቸውን ከአዲሱ የባሕል መመሪያ ጋር ለማስተካከል በመሻት መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት እንዲሰጣቸውና ትምህርት ቤትም እንዲከፈትላቸው ጠየቁ። በ1914 ዓ.ም. የባዘል ማኅበር አሥራ ስድስት ዋና ዋና ጣቢያዎች፥ ስልሳ ሰባት ሚስዮናውያን፥ ዘጠኝ ሚስዮናዊ እህቶች፥ 21,622 ተማሪዎች የሚገኙባቸው 384 ትምህርት ቤቶችና 15,112 የተጠመቁ አባላት ነበሩት።

ቀደም ብለን ያጠናነው ሌላ የፕሮቴስታንት ሚስዮን፥ ካሜሩን ውስጥ ሥራ ጀምሮ ነበር። ጋቦን ውስጥ ሥራ የጀመረው የአሜሪካ

ፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን የውጭ አገር ሚስዮናውያን ቦርድ፥ ጋቦን ውስጥ የጀመረው ተግባር በፈረንሳይ መንግሥት ምክንያት ችግር ቢገጥመው፥ በሰሜን አቅጣጫ ወደ ካሜሩን ይገፉ ጀመር። የሚስዮኑ አባላት ሥራቸውን የጀመሩት በ1890 ሲሆን፥ ወደ መሀል አገር የዘለቁት በ1892 ዓ.ም. ነው። የሚስዮኑ አባላት በአፍሪካ ምንም የቅኝ ግዛት ፍላጎት የሌላቸው የአሜሪካ ዜጎች ስለነበሩ፥ የጀርመን መንግሥት መልካም አቀባበል አደረገላቸው። የባዘል ሚስዮን ማኅበርም ክልሉን በሙሉ የሚያዳርስበት በቂ ሠራተኛ ስላልነበረው፥ የፕሬስቢቴሪያን ሚስዮን አባላት ደቡብ ምሥራቅ ካሜሩን ውስጥ መሥራታቸው ደስ አሰኝቶት ነበር። የፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን በ1914 ዓ.ም. ካሜሩን ውስጥ 5,000 የተጠመቁ አባላት ነበሯት።

በ1890 ዓ.ም. የሮም ካቶሊኮች ካሜሩን ውስጥ ሥራ ጀመሩ። የጀርመን መንግሥት ለፓየስ ሚስዮናውያን ማኅበር ቡድኖች ይህን ሥራ እንዲሠሩ ፈቀደላቸው። እነዚህ የካቶሊክ ሚስዮናውያን ወደ ስፍራው የደረሱት፥ ከፕሮቴስታንቶች እጅግ ዘግይተው ቢሆንም፥ ለጥምቀት የሚጠይቋቸው መመዘኛዎች ቀላል ስለነበሩ በ1914 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያኒቱ አሉኝ የምትላቸው አማኞች ቁጥር ከፕሮቴስታንቶች ጋር የሚስተካከል ነበር።

የጀርመን ቅኝ ገዢ መንግሥት፥ የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግሥታት እንዳደረጉት፥ ሚስዮናውያን ጠንካራ የሙስሊም ተጽዕኖ ባለበት ቦታ እንዲሠሩ አልፈቀደላቸውም። ምክንያቱም ቅኝ ገዢዎች ሁሉ ድርጊቱ ሙስሊሞችን የሚያስቆጣና ለአመጽ የሚያነሣሣ ነው ብለው ያስቡ ነበር። በመሆኑም ከ1878-1914 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ክርስትና ሰሜን ካሜሩን ውስጥ ወዳለው የእስልምና አካባቢ አልደረሰም ነበር።

ጋቦን

የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ጋቦን ክልል የደረሱት ከሮም ካቶሊካውያን በፊት እንደነበረ ምዕራፍ ሀያ አንድ ውስጥ ተመልክተናል። የፈረንሳይ ቅኝ ገዢዎች አገሪቱን ግዛታቸው ካደረጓት በኋላ ግን፥ ለፈረንሳይ ካቶሊካውያን የተሻለ ዕድል በመስጠት በምክርና በገንዘብ ይረዷቸው ጀመር። ከ1878-1914 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን ይበልጥ ታድግ ጀመር። በዚሁ መሠረት ካቶሊካውያን በ1856 ዓ.ም. አፍሪካውያን ካህናትን ማሰልጠኛ ሴሚናሪ ሊበርቪል ውስጥ አቋቋሙ። ነገር ግን እስከ 1899 ዓ.ም. ድረስ ትምህርቱን አጠናቆ ካህን የሆነ አፍሪካዊ አልነበረም።

የአሜሪካን ፕሬስቢቴሪያን ሚስዮናውያን ከቅኝ ገዢዎቹ በፊት ጋቦን የኖሩ ቢሆኑም፥ የፈረንሳይ ቅኝ ገዢዎች ስላስገደዷቸው

ጣቢያዎቻቸውን ጥለው ወጡ። ልክ እንደ ጀርመኖች ፈረንሳውያንም ቅኝ ግዛቶቻቸው ውስጥ እንዲሠሩ የሚፈልጉት የራሳቸው አገር ሚስዮናውያን እንዲሆኑላቸው ነበር። በ1890 ዓ.ም. የአሜሪካን ፕሬስቢቴሪያኖች በትምህርት ቤቶቻቸው ፈረንሳይኛ ያስተምርላቸው ዘንድ የወንጌላዊ ፓሪስ ሚስዮን ማኅበርን አገኙ። ቅኝ ገዢዎች የፈለጉት ግን የአሜሪካን ሚስዮናውያን ተጠቃለው እንዲለቁላቸው ስለነበር፥ ፕሬስቢቴሪያኖች ጋቦን ውስጥ የነበሯቸውን ጣቢያዎች በሙሉ ለፈረንሳይ የፕሮቴስታንት ማኅበር አስረከቡ። በ1913 ዓ.ም. የቀሩት የሚስዮን ጣቢያዎች ለፈረንሳውያኑ ማኅበር ተላለፉ። ፈረንሳውያኑም በዚህ ሁኔታ ተጀምሮ ያገኙትን ሥራ ማስፋፋት ቀጠሉ። በ1913 ዓ.ም. አምስት ጣቢያዎች፥ 1,908 ክርስቲያኖችና 1,976 የመሠረታዊ ክርስትና እምነት ተማሪዎች ነበሯቸው።

ጋቦንን ከመተዋችን በፊት የዚህን ክልል ሕዝብ ለመርዳት ስለመጣው አንድ ታዋቂ ሰው መግለጥ አለብን። ይህ ሰው አልበርት ስዋይትሰር ይባላል። አባቱ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ነበር። ልጅ ሳለ ሚስዮናውያን በአፍሪካ እንደሚያስፈልጉ ሰማ። በዩኒቨርስቲ ትምህርቱ በጣም ጥሩ ውጤት የነበረው ከመሆኑም ባሻገር፥ በጊዜው አርጋን የሚባለውን ሙዚቃ ጥሩ አድርገው ከሚጫወቱ ሰዎች አንዱ ነበር። የስዋይትሰር ደካማ ነገር በዩኒቨርስቲ ትምህርቱ ወቅት ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርቶች አንዳንዱን መጠራጠሩ ነበር። በእምነቱ ምክንያት ‘‘ሊበራል’’ (ለዘብተኞች) በመባል ከሚታወቁት የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሚመደብ ነው። ያም ሆኖ ወደ አፍሪካ በመሄድ ሕዝቡን ለመርዳት ይፈልግ ነበር። በዚሁ መሠረት ይህንኑ ፍላጎቱን በ1913 ዓ.ም. ለፓሪስ ሚስዮን ማኅበር አመለከተ። አንዳንድ የማኅበሩ ዳይሬክተሮች ሥር ነቀል ለውጥ ፈላጊ ምሁር ነው፥ በማለት ቢጠረጥሩትም ወደ ላምባሬኔ (ሚስዮን ጣቢያ) እንዲሠራ ተላከ። በዚያ የሚስዮን ጣቢያ ለአምሳ ዓመት ዶክተር ሆኖ አገለገለ።

የፈረንሳይ ኮንጎና ኡባንጊ ሻሪ ቻድ (የኮንጎ ሪፐብሊክ፥ የማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክና ቻድ)

የፈረንሳይ ኮንጎና ኡባንጊ ሻሪ ቻድ ከጋቦን ጋር በፈረንሳይ ቅኝ ገዢዎች ‘‘የፈረንሳይ ኢኳቶሪያል አፍሪካ’’ ተብለው ተሰየሙ። ከ1878-1914 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ፈረንሳይ ኢኳቶሪያል አፍሪካ ውስጥ የነበሩት የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን በተለይ በጋቦን የባሕር ዳርቻ ክልል ተወስነው ነበር። የሮም ካቶሊክ ሚስዮናውያን ግን ወደ መሀል አገር ዘለቁ።

ፈረንሳይ ኢኳቶሪያል አፍሪካ ውስጥ ላለው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሥራ በፓፓው የተመደቡት የፈረንሳይ የመንፈስ


ቅዱሳውያን አበው አባላት ነበሩ። በ1890 ዓ.ም. በኡባንጊ አዲስ የቤተ ክርስቲያን ስፍራ ተከለለ። ይህ ሥፍራ ለመንፈስ ቅዱሳውያን አበው የተሰጠ ሲሆን፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ገንዘብ የሚሰበስበው ካህን ከመሾሙ በፊት እርዳታው ከፈረንሳይ መንግሥት ይመጣ ነበር።

የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ እንደ ጋቦን፥ ኮንጎ፥ የማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ፥ እና ቻድ ባሉ አገሮች ከፍተኛ ሥፍራ የሚሰጣት መሆኑ የሚያስደንቅ አይደለም። የፈረንሳይ መንግሥት፥ ፈረንሳውያን ላልሆኑ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ሥራውን እጅግ ባከበደበት ጊዜ፥ ለፈረንሳይ ካቶሊካውያን ግን ለአብያተ ክርስቲያን እና ለሚስዮን ጣቢያዎች መገንቢያ የሚሆናቸው ከፍተኛ ገንዘብ ይሰጣቸው ነበር። በ1914 ዓ.ም. ዋዜማ በፈረንሳይ ኢኳቶሪያል አፍሪካ በአጠቃላይ 30,000 የሮም ካቶሊካውያን የነበሩ ሲሆን፥ አብዛኛዎቹ ጋቦን በነበረው የቤተ ክርስቲያኒቱ ሐዋርያዊ ተልዕኮ ኃላፊ ይመሩ ነበር።

የቤልጂግ ኮንጎ (ዛየር)

ከፕሮቴስታንቶች ቀድመው ኮንጎ ወንዝ ላይ ሥራ የጀመሩት፥ የሮም ካቶሊካውያን እንደነበሩ ምዕራፍ ሀያ አንድ ውስጥ ተመልክተናል። ሊዎፖልድ በኮንጎ ላይ በነበረው ፍላጎት ምክንያት እዚያ እንዲኖሩ የሚፈልገው የቤልጂግ ካቶሊክ ሚስዮናውያንን ብቻ ነበር። በፈረንሳይ ካቶሊካውያን ከተጀመሩት ሥራዎች አንዳንዶቹ የቤልጂግ ሚስዮናውያን ይቀጥሏቸው ዘንድ በመጠኑ መስተካከል ነበረባቸው። በዚህ ጊዜ ሊዎፖልድ የተገነዘበው ነገር፥ ይህን ሁሉ ሥራ ለመሥራት በቂ ቤልጂጋውያን ካቶሊኮች የሌሉት መሆኑን ነው። ስለዚህ ሌሎች አውሮፓውያን ወደ ኮንጎ እንዲገቡ ፈቀደ።

በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ገደማ ኮንጎ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ ባሉ ስፍራዎች ብዙ ሕዝቦች ይኖሩ ነበር። እነዚህ ወንጌል ያልደረሳቸው አፍሪካውያን፥ የሮም ካቶሊኮችና የፕሮቴስታንት ሚስዮን ማኅበራት በአካባቢው እንዲሠሩ ክፍት የአገልግሎት በር ሆኑላቸው። ንጉሥ ሊዎፖልድ ካቶሊካዊ በመሆኑ፥ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ኮንጎ ውስጥ እንድትስፋፋ ያበረታታት ነበር። በ1890ዎቹ ኢየሱሳውያን [Jesuit/ጀሱዊት] እና የኢየሱስ የተቀደሰ ልብ ማኅበር ሚስዮናውያን የሚስዮን ሥራ ጀመሩ። ከ1914 ዓ.ም. በፊት ወደ ቤልጂግ ኮንጎ የገቡት ተጨማሪ የሮም የካቶሊክ ወኪሎች ዝርዝር ሲታይ፥ ለሥራ የሚስቡ ሰፊ ንብረቶች መኖራቸውንና ለሥራው የመሰጠት ጉዳይ የተስፋፋ መሆኑን ያመለክታል። በ1894 ትራፒስቶች፥ በ1896 ፕሪሞንስትራቴንሲያኖች፥ 1899 ዓ.ም. ሪደምቶሪስቶች፥ 1905 ዓ.ም. የሚል ሂል አበው፥ በ1910



ዓ.ም. ቤነዲክትኖች እና ካፑቺኖች፥ በ1911 ዓ.ም. ዶሚኒካኖች እና ሳሊሲያኖች፥ በ1909 ዓ.ም. የክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ወንድማማቾች፥ በ1910 የጋንድ በጎ አድራጎት ወንድማማቾች፥ በ1911 የማሪስት ወንድማማቾች፥ በ1891 የጋንድ በጎ አድራጎት እህቶች ማኅበር፥ በ1895 የናሙር የእመቤታችን እህቶች ማኅበር፥ በ1895 ነጭ እህቶች፥ በ1896 የማርያም ፍራንሲስካን ሚስዮናውያን፥ በ1899 የቤርላሯ ማርያም የተቀደሰ ልብ እህቶች ማኅበር እና በ1911 ደግሞ የሌሻ መስቀል ሴቶች የተባሉት ድርጅቶች ገቡ። በ1914 ዓ.ም. ከሰሐራ በስተደቡብ በሚገኘው የአፍሪካ ክፍል ካሉ ማናቸውም የፖለቲካ አካላት የሚልቁ የተለያዩ የሮም ካቶሊካውያን የሆኑ የኮንጎ ተወላጆች ቡድኖች ሥራ ላይ ነበሩ። በ1914 ዓ.ም. እንደተገመተው የሮም ካቶሊካውያን የሆኑት የኮንጎ ተወላጆች ብዛት ከ100,000 በላይ ነበር።

የመጀመሪያው የፕሮቴስታንት ሚስዮን ምሥራቅ ኮንጎ ውስጥ ሥራ የጀመረው በ1878 ዓ.ም. ነው። ይህ ሚስዮን የሊቨንግስተን ኢንላንድ ሚስዮን በመባል ይታወቅ ነበር። የዚህ ሚስዮን ግብ በባሕሩ ዳር ከኮንጎ ወንዝ ጀምሮ እስከ ስታንሊ ፑል ድረስ ተቀባባይ የሚስዮን ጣቢያዎች ማቋቋም ነበር። አብዛኛዎቹ የቀድሞ ሚስዮናውያን በወባ ንዳድና ትኩሳት ቢሰቃዩም፥ በ1880 ዓ.ም. ሦስት የሚስዮን ጣቢያዎች ተቋቁመው ሠራተኞች ተመደቡላቸው። ሚስዮኑ ኮንጎ ወንዝ ላይ ለመቅዘፍ የሚያስችሉ ሁለት በእንፋሎት ኃይል የሚሠሩ ማጓጓዦችን ላከ። የሊቨንግስተን ኢንላንድ ሚስዮን እስከ 1883 ዓ.ም. አሥር የሚስዮን

ጣቢያዎች የነበሩት ሲሆን፥ ከነዚህ ራቅ የሚለው 1,280 ኪሎ ሜትር ወደ መሀል አገር የዘለቀ ነበር።

የሊቨንግስተን ኢንላንድ ሚስዮን የወንጌል ምስክርነቱን ኮንጎ ውስጥ በጀመረበት ወቅት፥ የእንግሊዝ ባፕቲስት ሚስዮናውያን ማኅበርም በአካባቢው ሥራ ለመጀመር በዝግጅት ላይ ነበር። በመጨረሻም ቀደምት ባፕቲስት ሚስዮናውያን ወደ ላይኛው የኮንጎ ወንዝ የሚወስድ መተላለፊያ አገኙ። መተላለፊያው ከስታንሊ ፑል በላይ የሚገኝ 1600 ኪሎ ሜትር የሚያህል ርቀት በጀልባ ሊኬድበት የሚያስችል ነበር። ሮበርት አርቲንግተን የተባለ ሰው በ1880 ዓ.ም. አንድ በጊዜውና በአካባቢው ግዙፍ የሆነ በእንፋሎት ኃይል የሚንቀሳቀስ መርከብ መግዣ የሚሆን አንድ ሺህ ፓውንድ ሰጠ። በእርግጥ ምሥጋና የሚገባው ልግስና ነው። ይህ 'ፒስ' ተብሎ የተሰየመ መጓጓዣ በመጨረሻ በስምንት መቶ ውልቅልቆች (ክፍሎች) ኮንጎ አካባቢ ደረሰ። ግሪንፍል ይህችኑ ማጓጓዣ በሚገባ ጠጋገነና በ1884 ዓ.ም. የመጀመሪያውን ጉዞ እንድታደርግ አስቻላት። ከዚህ የምንመለከተው፥ በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መርከቦች ወደ አፍሪካ የመጡበትን ሁኔታና በቀድሞ የቤተ ክርስቲያን ጅማሬ አዳዲስ ጣቢያዎች በመክፈት ረገድ በማጓጓዣነት ምን ያህል እንደጠቀሙ ነው።

በ1880ዎቹ ቀደምት ዓመታት፥ የሊቨንግስተን ኢንላንድ ሚስዮን ቀደም ሲል ኮንጎ ውስጥ ጀምሮት የነበረውን ሥራ ለአሜሪካን ባፕቲስት ሚስዮን ለማስረከብ ወሰነ። ይህ ሚስዮን ኮንጎ ወንዝ አካባቢ የነበሩትን የሊቨንግስተን ኢንላንድ ሚስዮን ጣቢያዎች በመውሰድ የራሱን አዳዲስ ጣቢያዎች የማቋቋም ሥራ ጀመረ። በ1886 ዓ.ም. የጥቁር አሜሪካውያን ባፕቲስት ሚስዮናውያን ይህን ሥራ ይበልጥ ለማሳደግ ኮንጎ ደረሱ።

የእንግሊዝና የአሜሪካን ባፕቲስት ሚስዮናውያን ማኅበራት ተልዕኮ የተሳካ መሆኑን የተመለከቱ ሌሎች የአሜሪካን ሚስዮናውያን ወደ አገልግሎቱ ተሳቡ። በዚሁ መሠረት የአሜሪካ መቶዲስት ቤተ ክርስቲያን በ1886 ዓ.ም. ኮንጎ ውስጥ ሥራውን ጀመረ። በ1889 ዓ.ም. የመጀመሪያዎቹ የክርስቲያንና የሚስዮን ትብብር በመባል የሚታወቀው ቡድን ሚስዮናውያን ኮንጎ ውስጥ የተዋጣለት ጣቢያ አቋቋመ። የቤልጂግ ኮንጎ በመባል የሚታወቀው ስፍራ በጣም ሰፊ ክልል በመሆኑ፥ እዚያ ለሚገኙት ሰዎች ሁሉ ወንጌልን ለማዳረስ ተጨማሪ የሚስዮን ድርጅቶች አስፈለጉ። በመሆኑም የአሜሪካ ፕሬስቢቴሪያን በመባል የምትታወቀው ቤተ ክርስቲያን በ1891 ዓ.ም. እስፍራው የሚስዮን ጣቢያ ከፈተች።*

* የዚህ መጽሐፍ ደራሲ የሩቅ ዘመድ የሆነው ሳሙኤል ሳፕስሊ፥ ከፕቁር አሜሪካዊ ሚሊያም ሼፐርድ ጋር በ1890 ወደ ኮንጎ ገባ። ብዙም ሳይቆይ ሳፕስሊ በወባ በሽታ ተይዞ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ሼፐርድ፥ ወደ አሜሪካን እስከተመለሰበት እስከ 1911 ድረስ ኮንጎ ውስጥ መኖርና መሥራት ቀጠለ።

በ1895 ዓ.ም. ደግሞ የአሜሪካ የክርስቶስ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የሚባለው ቡድን ሥራውን ጀመረ። በዚሁ ዓ.ም. ኮንጎ ውስጥ ሥራቸውን የጀመሩት ሌሎች ሚስዮናውያን የፕሊመስ ወንድማማቾች፥ የኮንጎ ኢንላንድ ሚስዮን (ሚነናይት) እና የአሜሪካ ደቡባዊ መቶዲስቶች ነበሩ። ከምዕራብ አፍሪካ ጋር ሲነጻጸር፥ በዚህ ወቅት የአሜሪካን ሚስዮን ማኅበራት ኮንጎ ውስጥ የበዙበት ምክንያት፥ ንጉሥ ሊዎፖልድ ፈረንሳውያን ወይም ጀርመኖች ያደርጉት ይሆናል ብሎ እንዳሰበው፥ አሜሪካውያን ነጻ ግዛቱን ለመውሰድ ይሞክሩ ይሆናል የሚል ፍርሃት ስላላደረበት ነው።

በማጥናት ላይ ባለነው ክፍለ ዘመን (ከ1878-1914 ዓ.ም. ማለት ነው) መጨረሻ አካባቢ፥ ኮንጎ ውስጥ ለመሥራት የሚያስችል አዲስ የመግቢያ ስፍራ ተከፍቷል። ከ1910 ዓ.ም. በፊት አብዛኛዎቹ የሚስዮን ማኅበራት ወደ ቤልጂግ ኮንጎ ለመግባት የሚገለገሉት በኮንጎ ወንዝ ነበር። በ1909 ዓ.ም. ግን የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ዋና ኃላፊ የነበሩት ሚስተር ሲ. ኤ. ሐርልበርት የወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ቴዎዶር ሩዝቬልት የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ወደ ቤልጂግ ኮንጎ ምሥራቃዊ አዋሳኝ በመግባት፥ ሥራ እንዲጀምር የቤልጂግን መንግሥት ያስፈቅዱላቸው ዘንድ ጠየቋቸው። በዚሁ መሠረት የቤልጂግ መንግሥት ተስማማና የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን በምሥራቅ በኩል ወደ ኮንጎ ገብቶ የክርስትና ሥራ በመጀመር ረገድ የመጀመሪያው ድርጅት ሆነ። በ1910 ዓ.ም. የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን አንድ አጥኚ ቡድን ወደ ምሥራቅ ኮንጎ በመላክ፥ በዚያ የሚስዮን ጣቢያ ለመክፈት የሚቻል መሆን አለመሆኑን አስጠና። የመጀመሪያዎቹ ቋሚ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ሚስዮናውያን በ1912 ዓ.ም. ኮንጎ ውስጥ ድንኳናቸውን ተክለው ሥራ ጀመሩ።

በ1913 ዓ.ም. ደግሞ የመሀል አፍሪካ ሚስዮን በመባል የሚታወቅ አዲስ የሚስዮን ማኅበር ተቋቋመ። ሲ. ቲ. ስተድ የተባለው ታዋቂ ሚስዮናዊና አብሮት የሚሠራ ጓደኛው ከምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ዳርቻ ተነሥተው ወደ ምሥራቅ ኮንጎ በመጓዝ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን የሚስዮን ጣቢያ ከነበረበትና ዱንጉ ከተባለ ስፍራ 80 ኪሎ ሜትር ርቀው ሥራቸውን ጀመሩ። ኮንጎ በደረሱ ጊዜ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ሥራ እንዲጀምር ፈቃድ ቢያገኝም፥ ለሌላ ሚስዮን ግን እንዲህ ዓይነቱ የመግቢያ ፈቃድ እንደማይሰጥ ተነገራቸው። ስለዚህ በአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ከለላነት መግባት እንዳለባቸውና ከገቡ በኋላ የተለየ አካል ለመመሥረት ከፈለጉ ግን ያን ለማድረግ ነጻ መሆናቸው ተረጋገጠላቸው።

ኮንጎ ውስጥ ስለተሠራው ክርስቲያናዊ ሥራ አጭር ጥናት ያደረግንበትን ይህን ክፍል ስናጠቃልል፥ ቤተ ክርስቲያን የኮንጎን ሕዝብ

ለመርዳት የተጫወተችውን ቁልፍ ሚና መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ንጉሥ ሊዎፖልድም ሆነ፥ የኋለኞቹ የቤልጂግ መንግሥት ሰዎች ምንም ትምህርት ቤቶች አልከፈቱም። በመሆኑም ማንኛውም የትምህርት ጉዳይ የመጣው በሚስዮን ትምህርት ቤቶች አማካይነት ነው። አብዛኛዎቹ ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች የሚመሩት በሚስዮን ማኅበራት ነበር። በዚህ ጊዜ የነበሩ ክርስቲያኖች ከፍተኛ አስተዋጽኦ፥ የኮንጎ ፍሪ ስቴትን ከንጉሥ ሊዎፖልድ የመውሰድ እንቅስቃሴ ነበር።

የሊዎፖልድን ቅጥረኛ ወታደሮች እጅግ የከፋ ባሕርይ፥ እንዲሁም ንጉሡ ይጠይቀው የነበረውን ተገቢ ያልሆነ ቀረጥ ለመመልከት የቻሉና ለዓለም ሕዝብ ያሳወቁት ኮንጎ ውስጥ ይሠሩ የነበሩት የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ናቸው። የነዚህ ሚስዮናውያን ዋና ፍላጎት፥ አፍሪካውያኑ ሊዎፖልድ ኮንጎን የያዘበትን ተገቢ ያልሆነ መንገድ አስመልክቶ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያሰሙ ማድረግ ነበር። በመጨረሻም በ1908 ዓ.ም. የተከሰተው የዓለም አመለካከት የቤልጂግ መንግሥት የኮንጎን ነጻ አስተዳደር ከንጉሥ ሊዎፖልድ እንዲወሰድ አስገደደው። ከዚህ በኋላ ቤልጂግ ኮንጎ ውስጥ ያለው የአፍሪካውያን አኗኗር ሁኔታ በጥቂቱ ተሻሻለ።

አንጎላ

ከዚህ ቀደም የአንጎላን ታሪክ ስንመለከት፥ በክልሉ ይሠሩ የነበሩት የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ብቻ እንደነበሩ ተገንዝበናል። ብዙው ሥራ በባሕር ዳርቻው በሚገኙ ሦስት ዋና ከተሞች ላይ ያተኮረ ነበር። በ1879 ዓ.ም. የመንፈስ ቅዱሳውያን አበው ደቡብ አንጎላ ውስጥ ሥራ እንዲጀምሩ በፓፓው ፈቃድ ተሰጣቸው። እነዚህ ሰዎች ከፖርቱጋል ሚስዮናውያን ይበልጥ የሥራ መነሣሣትና መነቃቃት በማሳየት፥ ወዲያውኑ ትምህርት ቤቶችን፥ ዕጓለሙታን ማሳደጊያዎችን፥ ሆስፒታሎችን፥ አፍሪካውያን ካህናትን የማሰልጠኛ ሴሚናሪና የጀማሪ አገልጋዮች ማሰልጠኛ ስፍራዎችን አቋቋሙ። ከእነዚህ ሥራዎች አብዛኛዎቹ የሚካሄዱት የፖርቱጋል መንግሥት ለሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በሚሰጠው ገንዘብ ነበር። በ1913 ዓ.ም. የመንፈስ ቅዱሳውያን አበው አንጎላ ውስጥ የአገሪቱ ተወላጆች የሆኑ 29,200 ካቶሊካውያን አባላትን መዘገቡ።

የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ወንጌል ለመስበክ መጀመሪያ አንጎላ የገቡት በ1878 ዓ.ም. ነበር። የመጀመሪያው ሚስዮን አባላት ዋና መሥሪያ ቤቱን ሳንሳልቫዶር በተባለው ስፍራ ያደረገው የእንግሊዝ ባፕቲስቶች ናቸው። ለውጭ ሚስዮናዊ ተልእኮ የአሜሪካ ኮሚሽነሮች ቦርድ የሚስዮን

ጣቢያ የተመሠረተው በ1880 ዓ.ም. ቤንጉዌላ በሚባለውና መሀል አገር በሆነው በቢሄ ነው። እነዚህን ሚስዮናውያን ተከትለው ወደ ስፍራው የመጡት፥ ካናዳውያን ኮንግሬጌሽናሊስቶች (1886 ዓ.ም.)፥ የፕሊመስ ወንድማማቾች (1899 ዓ.ም.)፥ የአንጎላ ወንጌላዊ ሚስዮን (1897 ዓ.ም.)፥ የክርስቲያንና የሚስዮን ትብብር (1910 ዓ.ም.)፥ እና የደቡብ አፍሪካ አጠቃላይ ሚስዮን (1914 ዓ.ም.) የተባሉት ናቸው። የእነዚህ ፕሮቴስታንታዊ ሚስዮናውያን ከፖርቱጋል መንግሥት እርዳታ ባለማግኘታቸው እድገታቸው የተወሰነ ነበር። ያም ሆኖ የመንገድ ከፋችነት ሚስዮናዊ ሥራ ያከናውኑ ነበር። በዚህም ለሚመጡት ዓመታት የወንጌል ሥራ ቀጣይ የሚሆን መሠረት በ1914 ዓ.ም. ተጣለ።

ጥያቄዎች

1. የካሜሩን ባፕቲስት ሚስዮን በ1886 ዓ.ም. ሥራውን ለባዘል ሚስዮን ያስረከበው ለምን ነበር?

2. የአሜሪካን ፕሬስቢቴሪያኖች ጋቦን ውስጥ የነበራቸውን ሥራ የተውት ለምን ነበር? መቼ ነው ይህ የሆነው?

3. ቤልጂግ ኮንጎ ውስጥ ሥራ የጀመረ የመጀመሪያው የፕሮቴስታንት ሚስዮን (ቤልጂግ ኮንጎ በዚያን ጊዜ የኮንጎ ፍሪ ስቴት ይባል ነበር) የቱ ነበር? መቼ ነው ሚስዮኑ ሥራ የጀመረው?

4. የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ቤልጂግ ኮንጎ ውስጥ ሥራ የጀመረው መቼ ነበር?

5. ከ1910 ዓ.ም. በፊት የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ኮንጎ ውስጥ የሚኖሩትን አፍሪካውያን የረዷቸው በምን አኳኋን ነው?

6. አንጎላ ውስጥ መጀመሪያ ሥራ የጀመረው የፕሮቴስታንት ሚስዮን ማኅበር የቱ ነበር? የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን ይልቅ በፍጥነት ያደገችው ለምን ነበር?

ደቡብ አፍሪካ ውስጥ እድገቱ ቀጠለ 1878-1914 ዓ.ም.

ደቡብ ምዕራብ አፍሪካ

የደቡብ ምዕራብ አፍሪካ ክልል የጀርመን ቅኝ ግዛት የሆነው በ1885 ዓ.ም. ነበር። ይህ ክልል ካርታ ላይ ትልቅ ቢመስልም፥ የሕዝቡ ቁጥር ግን አነስተኛ ነበር። የክልሉ አብዛኛው ክፍል ብዙ ሕዝብ ማኖር የማይችል በረሃማ ነው። በ1900 ዓ.ም. የግዛቱ ሕዝብ ብዛት ወደ 200,000 ገደማ ነበር።

ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የነበረውን ቀዳሚ የሚስዮናውያን ሥራ እድገት በተመለከትን ጊዜ፥ ደቡብ ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ የነበረውን የቤተ ክርስቲያን አጀማመር አይተናል። የኦሬንጅን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ታላቋ ናማኳላንድ በመውጣት የመጀመሪያውን ክርስቲያናዊ ሥራ በ1842 ዓ.ም. የጀመረው የሬኒሽ ሚስዮናዊ ማኅበር ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ በወንጌል ሥራ በጥሩ ሁኔታ የገፋችው በ1870 ዓ.ም. ነበር። አዲስ የፕሮቴስታንት ሚስዮን እስፍራው የደረሰውም በዚሁ ጊዜ ነው። ይህም የፊንላንድ ሚስዮናዊ ማኅበር በመባል ይታወቅ ነበር። የዚህ ሚስዮን አባላት በክልሉ ሰሜናዊ ክፍል አቫምቦ በተባሉት ነገዶች መካከል ሥራቸውን ጀመሩ። በ1880ዎቹ ዓመታት ክርስቲያናዊ ሥራን አስቸጋሪ ያደረጉ ብዙ የነገድ ጦርነቶች ይካሄዱ ነበር።

ሬኒሽ ሚስዮን ውስጥ የነበሩ የጀርመን ሚስዮናውያን፥ ጀርመን ደቡብ ምዕራብ አፍሪካን አንድ በማድረጓ መጀመሪያ ደስ ተሰኝተው ነበር። ጀርመኖች እርስ በእርስ ለሚዋጉ ነገዶች ሰላምን በማምጣት፥ መንገዶችን በመሥራት፥ የፖስታ ግንኙነትን በመፍጠር፥ ወዘተ...ግዛቲቱን ያሳድጓታል ብለው አሰቡ። ሆኖም ብዙ ሳይቆዩ ነው የጀርመን ቅኝ ገዢዎች እጅግ ጥብቅ አስተዳዳሪዎች መሆናቸውን የተገነዘቡት። የጀርመን ሠፋሪዎች የምድሪቱን አንዳንድ ክፍሎች ያርሱ ጀመር። እነዚህ ነጭ ሠፋሪዎች የክልሉን መልካም መሬቶች በሙሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከአፍሪካውያኑ እንደሚወስዱባችው የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ተገነዘቡ። ስለዚህ የቅኝ ገዢ አውሮፓውያኑን አስተዳደር በሩቁ ለመከላከል ይቻል ዘንድ አንዳንድ መሬቶችን ለአፍሪካውያኑ እንዲተው አስገደዷቸው።

በ1903 ዓ.ም. የሄሬሮ ነገድ አባላት በጀርመን ቅኝ ገዢዎች ላይ አመጹ። ብዙ አውሮፓውያን አስተዳዳሪዎችንና ጀርመናውያን ነጭ ሠፋሪዎችንም ገደሉ። በዚህም የተነሣ የጀርመን መንግሥት ጭካኔ

በተሞላበት ሁኔታ ሄሬሮዎችን ወጋቸው። በጦርነቱ ብዙ ሰላማዊ ሰዎች ሞቱ። ወዲያውኑ በክልሉ ያሉ የሆቴንቶ ጎሳ አባላት ጀርመንን በሚቃወመው ጦርነት ውስጥ ተቀላቅለው ነበር። ያም ቢሆን በ1907 ዓ.ም. ጀርመናውያን አፍሪካውያኑን ድል አደረጓቸው። በነገድ የተደራጁት ሄሬሮችና ሆቴንቶቶች የተደመሰሱት፥ ጦርነቱ እጅግ የተጋጋለና ጭካኔ የተሞላበት ስለነበር ነው።

ይህ ጦርነት በቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ችግር አምጥቶባታል። ምድራቸውን እንዲያስመልሱ አፍሪካውያንን በጦርነቱ በማበረታታት ረድታችኋቸዋል ብለው ቅኝ ገዢዎችና ሠፋሪዎች አንዳንድ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያንን ወነጀሏቸው። ብዙ የሄሬሮ ጎሳ አባላትም አውሮፓውያንን በሙሉ ከመጥላታቸው የተነሣ፥ ወንጌል የሚሰብኩ ሚስዮናውያንን እንኳ አንሰማችሁም አሏቸው።

የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ደቡብ ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ ከፍተኛ እድገት ማሳየት የጀመረችው ከ1907 ዓ.ም. በኋላ ነው። ካቶሊኮች ሥራቸውን የጀመሩት ቀደም ሲል በ1892 ዓ.ም. ቢሆንም ከክልሉ ነዋሪዎች ወደ እምነቱ የተለወጡት በጣም ጥቂት ነበሩ።

በ1914 ዓ.ም. እንደተገመተው፥ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አባላት ቁጥር 5,000፥ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን አባላት ቁጥር ደግሞ ከ10,000 በላይ ነበር።

ቤቹዋናላንድ (ቦትስዋና)

የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር በሮበርት ማፈት አመራር የቤቹዋናላንድን እንዴት ለወንጌል እንደከፈተ ቀደም ብለን ምዕራፍ አሥራ አራት ውስጥ ተመልክተናል። ቤቹዋናላንድ በአንድ መልኩ ልክ እንደ ደቡብ ምዕራብ አፍሪካ ነበር። አብዛኛው ክፍል ምድረ በዳ ወይም ከፊል ምድረበዳ ነው። ከክልሉ መጠን ጋር ሲወዳደር የሕዝቡ ቁጥር አነስተኛ ነበር። ስለሆነም እንደ ሌሎቹ ክፍሎች (ለምሳሌ ቤልጂግ ኮንጎ) ብዙ ሚስዮናውያን በስፍራው አልተሰማሩም። አሁን በምንመለከተው ጊዜ ቤቹዋናላንድ ውስጥ የነበረው ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ድርጅት የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር ነበር። የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበርን ሥራ በማገዝ በጥምር የሠሩት ደግሞ፦ የዌስሊየን መቶዲስት ሚስዮን፥ የፓሪስ ወንጌላዊ ሚስዮናውያን ማኅበር፥ እና የሆላንድ ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። ከ1914 ዓ.ም. በፊት በስፍራው ቋሚ ሆኖ የሚሠራ የሮም የካቶሊክ ሚስዮን አልነበረም።

ከ1878-1914 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ብዙ አፍሪካውያን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው እየተቀበሉ የቤተ ክርስቲያን እድገት

ቀጠለ። ይህ ጊዜ የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር አፍሪካውያንን ለመርዳት በትጋት የሠራበት ወቅት ነበር። ትምህርት ቤቶችና ሆስፒታሎች ተገነቡ። የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር አፍሪካውያንን የረዳበት ሌላ መንገድ፥ ሲስል ሮድስ ከተባለው ስግብግብ ኩባንያ ድርጊት ሕዝቡን መጠበቅ ነው። ጀርመን በደቡብ ምዕራብ አፍሪካ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ስታነሣ፥ ታላቋ ብሪታንያም በ1885 ቤቹዋናላንድን በቁጥጥርዋ ሥር ለማድረግ ፈለገች። ነገር ግን ሲስል ሮድስ የቤቹዋናላንድን የተወሰነ ክፍል ታላቋ ብሪታንያ እንድትሰጣትና አዲስ ግዛቷ ከሆነው ሮዴሽያ ጋር ልትቀላቀለው ፈለገች። የአካባቢው የነገድ አለቆች በጉዳዩ ያልተደሰቱ መሆናቸውን የተረዳው የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር፥ በ1895 ዓ.ም. ሦስት የነገድ አለቆች ወደ እንግሊዝ እንዲሄዱና ችግሩን ለንግሥቲቱ በግልጥ እንዲያስረዱ ለማድረግ ሞከረ። የሦስቱ የነገድ አለቆች ፍርሃት፥ ነጭ ሠፋሪዎች ምድራችንን ለመውሰድ ይሞክራሉ፥ የማይታመኑ ነጋዴዎቻቸውም ሰዎቻችንን ያታልሉብናል፥ የአልኮል መጠጥ ወደ ስፍራው ማምጣታቸውንም ይጨምራሉ የሚል ነበር። የአልኮልን አደገኛነት የተረዳው አንዱ አፍሪካዊ የጎሳ አለቃ ለእንግሊዝ አስተዳዳሪዎች እንዲህ በማለት ነገራቸው፦ ‘‘አገሬ በመጠጥ ጎርፍ ስትጥለቀለቅ ከማይ ብለያት እመርጣለሁ። ከሎቤንጉላ ይልቅ፥ ብራንዲ የተባለውን መጠጥ እፈራለሁ። ሰዎችን ከሚገድለው የማታቢሌ ጦር ይልቅ የነጮችን መጠጥ ከልቤ እጠላለሁ... መጠጥ በሰዎች ውስጥ ዲያብሎስ በማስገባት ነፍሳቸውንና ሥጋቸውን ለዘላለም ያጠፋል። ቁስሉ ፈውስ የለውም። ክቡርነትዎን የምማጸነው፥ በትንሹም ቢሆን እንኳን ለመጠጥ ማስገቢያ የሚሆን በር እከፍት ዘንድ እንዳትጠይቁኝ ነው።’’ በእነዚህ አለቆች ንግግርና በለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር ሚስዮናውያን ድጋፍ ሲስል ሮድስ ወደ ቤቹዋናላንድ እንዳይገባ ታገደ።

ደቡብ አፍሪካ

የደቡብ አፍሪካ ቤተ ክርስቲያን በ1880 ዓ.ም. አህጉሪቱ ውስጥ ከሚገኙት ሌሎች አብያተ ክርስቲያን ይልቅ አደገች። አፍሪካውያን የቤተ ክርስቲያን ካህናት በዙ፤ ብዙዎቹ የእምነት ክፍሎችም ራሳቸውን ለማስተዳደር ይችሉ ነበር። ከሕዝቡ ከመቶ አብዛኛው እጅ ክርስቲያን እንደሆነ ይታሰብ ነበር። ይህ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሁኔታ መልካም ቢመስልም፥ ከ1880 ዓ.ም. በኋላ ያጋጠማት ችግር ለላቀ እድገት የነበራትን ተስፋ አደበዘዘው። ትልቁ ችግር በነጭ ሠፋሪዎችና በአፍሪካውያኑ መካከል የነበረው ግጭት ነበር።

ከ1878-1914 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ብዙ አዳዲስ የፕሮቴስታንት ሚስዮኖች ደቡብ አፍሪካ ውስጥ መሥራት ጀምረው ነበር። ከነዚህ ብዙዎቹ

ከስካንዲኔቪያን አገሮች የመጡ ሲሆኑ፥ ትኩረታቸው ዙሉላንድን በወንጌል መድረስ ነው። ሌሎቹ ከአሜሪካ (ዩናይትድ ስቴትስ) የመጡ ናቸው። በ1889 ዓ.ም. የደቡብ አፍሪካ አጠቃላይ ሚስዮን ተመሠረተና ሥራው ከደቡብ አፍሪካ ወደ ሌሎች አገሮች በፍጥነት ተስፋፋ። የደቡብ አፍሪካ አጠቃላይ ሚስዮን፥ ዛሬ የአፍሪካ ወንጌላዊት ጎብረት ተብሏል።

በ1892 ዓ.ም. የዌስሊየን መቶዲስት መጋቢ የነበረውና ማንገና ኤም. ሞኮኔ የተባለው ሰው፥ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ከሚገኝ የዌስሊየን ሚስዮናውያን ጋር ያለመግባባት ፈጠረ። ያለመግባባቱ ምክንያት የመቶዲስት ቤተ ክርስቲያን በተገቢው ፍጥነት በአፍሪካውያን እጅ ሥር እየሆነች አልመጣችም የሚል ነበር። በዚህ የተነሣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ተነጥሎ ለመውጣት ወሰነ። ከዚያም እራሷን የቻለች ቤተ ክርስቲያን በማቋቋም፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በማለት ሰየማት። ይህን ድርጊት በትኩረት መመልከቱ እጅግ ይጠቅማል። ምክንያቱም በዘመናዊው ዓለም የመጀመሪያይቱን ሴፐሬቲስት ወይም ነጻ አፍሪካዊት (ጥገኛ ያልሆነች) ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት የሚያመለክት በመሆኑ ነው። ብዙም ሳይቆይ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የነበሩ ሁለት ወይም ሦስት ሌሎች የአፍሪካ መጋቢያን ተለይተው የወጡ አብያተ ክርስቲያንን አቋቋሙ። ወደፊት በምንመለከታቸው ምዕራፎች የነዚህ አብያተ ክርስቲያን ቁጥር እየጨመረ የሄደበትን ሁኔታ እናያለን።

የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በዚያ ጊዜ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ያሳየችው እድገት አዝጋሚ ነበር። መጠነኛ እድገት የታየው በነታል እና ኬፕ ኮሎኒ ነው። ኦሬንጅ ፍሪ ስቴት የሞግዚት አስተዳደር በሆነችው ቤቹዋናላንድ ውስጥ የነበሩት የአገሪቱ ተወላጅ ካቶሊካውያን ቁጥር በ1914 ዓ.ም. እጅግ አነስተኛ ነበር። ትራንስቫል ውስጥም በዚሁ ዓመተ ምሕረት የነበረው ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይደለም። በተጣበበችው የጆሃንስበርግ የማዕድን ከተማ ውስጥ እንኳ የተሰበሰቡት ጥቁር የሮም ካቶሊካውያን እጅግ ጥቂት ነበሩ።

ይህን ክፍል የምናጠቃልለው፥ የደቡብ አፍሪካን ፖለቲካዊ ታሪክ በመጥቀስ ሊሆን ይገባል። የእንግሊዝ መንግሥት በ1910 ዓ.ም. ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ይገኙ የነበሩ አውሮፓውያን በርሷ ሙሉ የበላይነት ሥር ራሷን የምታስተዳድርና የተባበረች የደቡብ አፍሪካ መንግሥት እንዲመሠርቱ ረዳቻቸው። ለአውሮፓውያን ራስን የማስተዳደር መብት መስጠቱ፥ በጥቁሮችና ነጮች መካከል የነበረውን ችግር ከፍተኛ ደረጃ ላይ አደረሰው። በመሆኑም፥ በጊዜው የማያስደስት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህን ሁኔታ ዘግየት ብለን እንመለከተዋለን።

ሞዛምቢክ

ሞዛምቢክ ለብዙ ምዕተ ዓመታት የፖርቱጋል ቅኝ ሆናለች። በ1878 ዓ.ም. ግን እዚያ የነበረችው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በጣም ትንሽ ነበረች። አባላቷም በባሕሩ ዳር የሚገኙ ነጭ ባለሥልጣኖች ብቻ የነበሩ ይመስላል። ፖርቱጋሎች በ1850 ዓ.ም. አካባቢ የካቶሊክ ሚስዮናውያንን በሙሉ አባረሯቸው። እስከ 1881 ዓ.ም. ድረስ አንዳንድ ኢየሱሳዊ (Jesuit/ጀሱዊት) ሚስዮናውያን እንኳ እንደገና ወደ ሞዛምቢክ ለመግባት አልቻሉም ነበር። በ1914 ዓ.ም. በግዛቲቱ የነበሩት የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ብዛት አምስት ሺህ ያህል ብቻ ነበር።

ሞዛምቢክ ውስጥ የመጀመሪያው የፕሮቴስታንት ሚስዮን ሥራ ጀማሪ፥ የስዊዘርላንድ ፕሮቴስታንት ሚስዮን ነበር። የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያናቸው የተመሠረተው፥ ትራንስቫል በሚገኘውና ከጣቢያዎቻቸው አንዱ በሆነው ስፍራ በወንጌላዊነት በሰለጠነ አንድ አፍሪካዊ ነበር። በ1879 ዓ.ም. ለውጭ ሚስዮናዊ ተልእኮ የአሜሪካ ኮሚሽነሮች ቦርድ ሚስዮናውያንን ወደ ግዛቲቱ ላከ። ከነበረው መጥፎ የአየር ሁኔታ የተነሣ፥ እስከ 1883 ዓ.ም. ድረስ በስፍራው ቋሚ ጣቢያ አልተመሠረተም። ወደ ሞዛምቢክ የመጡት ሌሎች የፕሮቴስታንት ሚስዮናዊ ነጻ መቶዲስቶች፥ የመቶዲስት ኤጲስ ቆጶስ፥ እና የእንግሊዝ አብያተ ክርስቲያን ናቸው።

ደቡባዊ ሮዴሽያ (ዚምባብዌ)

አሁን ዚምባብዌ በመባል የሚታወቀው ክልል በእንግሊዝ ጥበቃ ውስጥ የገባው፥ በአሥራ ዘጠነኛው መቶ መጨረሻ ዓመታት በሲስል ሮድስ ሥራ ምክንያት ነበር። ሮድስ የእርሻና የማዕድን ሥራ ለማከናወን ብዙ ነጭ ሰፋሪዎችን ወደ ስፍራው አመጣ። በ1900 ዓ.ም. በክልሉ ይኖሩ የነበሩ አፍሪካውያን ቁጥር ሁለት ሚሊዮን ይደርስ ነበር።

ክርስትና ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ስፍራው የመጣው፥ ቀደምት የፖርቱጋል ሚስዮናውያን ወንጌልን ወደ ዚምባብዌ ለመውሰድ በሞከሩበት በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። ጥረቱ ግን ዘላቂ ውጤት አላስገኘም። እንደገና ቋሚ የሚስዮን ጣቢያ የተቋቋመው ሮበርት ማፊት የሚስዮናውያንን ቡድን በመምራት ወደ ክልሉ በገባበት በ1859 ዓ.ም. ነው። የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር ለሠላሳ ዓመታት ሮዴሽያ ውስጥ ቢሠራም፥ ወደ ክርስቶስ ያመጣቸው ሰዎች ብዙ አልነበሩም። የእንግሊዝ ገዢ ከመምጣቱ ጋር አስደናቂ ለውጥ ተከናወነ። የአገሬው ሕዝብ የነጩን አገዛዝ ለመልመድ ፍላጎት ስላደረበት፥ ነጭ መምህራንን የማግኘት ጉጉት ነበር። በዚሁ መሠረት በሀያኛው ምዕተ ዓመት የመጀመሪያ አሥር

ዓመታት፥ የትምህርት ቤቶችና የቤተ ክርስቲያን አባላት ቁጥር ከፍተኛ እድገት አሳየ።

የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን በ1891 ዓ.ም. ሮዴሽያ ውስጥ ሥራዋን ጀመረች። በቀደምት ሚስዮናውያን ከፍተኛ ጥረት ብዙ አዳዲስ የቤተ ክርስቲያን አባላት ተገኙና ወዲያውኑ በአባላት ቁጥር ብዛት በዚህች ግዛት ያለች ትልቅ ቤተ ክርስቲያን የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሆነች።

ሮዴሽያ ውስጥ ወንጌልን ለማሰራጨት የነበረው መልካም ዕድል፥ ሌሎች ብዙ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ድርጅቶችን የሚስብ ሆነ። የዌስሊያን መቶዲስቶች (በ1891 ዓ.ም.)፥ የሆላንድ ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን (በ1891 ዓ.ም.)፥ ለውጭ ሚስዮናዊ ተልእኮ የአሜሪካ ኮሚሽነሮች ቦርድ (በ1893 ዓ.ም.)፥ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስቶች (በ1895 ዓ.ም.)፥ የአሜሪካ መቶዲስት ኤጲስ ቆጶሳዊ ቤተ ክርስቲያን (በ1896 ዓ.ም.)፥ የክርስቶስ ወንድማማች (በ1897 ዓ.ም.)፥ የደቡብ አፍሪካ አጠቃላይ ሚስዮን (በ1897 ዓ.ም.)፥ ኋላ ደግሞ የፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን፥ የደኅንነት ሠራዊት እና የስዊድን ቤተ ክርስቲያን ሥራ ጀመሩ።

የሮም ካቶሊኮች በ1889 ዓ.ም. ደቡባዊ ሮዴሽያ ውስጥ ቋሚ ሥራ ጀመሩ። በ1914 ዓ.ም. ሌሎች ሁለት የካቶሊክ ሚስዮን ማኅበራት ከዚህ ሥራ ጋር ተጣምረው ተግባራቸውን ቀጠሉ። ያም ሆኖ ወደ እምነቱ የሚመጡ ሰዎች ቁጥር በፍጥነት አልጨመረም።

ሰሜናዊ ሮዴሽያ (ዛምቢያ)

ሰሜናዊ ሮዴሽያ ውስጥ የመጀመሪያው ሥራ የተከፈተው በ1878 ዓ.ም. በለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር ነው። በዚህ ሥራ አማካይነት የተገኘው ቋሚ የሚስዮን ጣቢያ በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል በታንጋኒካና በማላዊ ሐይቅ መካከል ነበር። በታንጋኒካ ሐይቅ ዳርቻ የነበሩ አንዳንድ የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር ጣቢያዎች በኋላ ቢዘጉም፥ በከፍተኛ አካባቢዎች ሌሎች ጣቢያዎች ተከፈቱ። ስለዚህ የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር በ1914 ዓ.ም. ትምህርት ቤቶች፥ አብያተ ክርስቲያን፥ የኢንዱስትሪ ማሰልጠኛዎችና የሕክምና መስጫ ማዕከላት አቋቋሙ።

የሮም ካቶሊኮች በ1891 ዓ.ም. ሰሜን ሮዴሽያ ውስጥ ሥራ ጀመሩ። በዚሁ መሠረት በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል በሚገኙት የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር ጣቢያዎች አቅራቢያም ለመሥራት ሞክረዋል። በ1905 ዓ.ም. ደግሞ ሌላ የሮም ካቶሊክ ሚስዮን ግዛቲቱ ውስጥ ሥራ ጀመረ።

በ1890ዎቹ ዓመታት የእንግሊዝ ጥንታዊ የእንግሊዝ መቶዲስት ሚስዮን፥ በግዛቲቱ የደቡብ ምዕራብ ክልል ሥራ ጀመረ። ቀደም ብለው


የመጡት ሚስዮናውያን የሕዝቡን ቋንቋ በመማር የቋንቋውን ሰዋሰው ጻፉ። እንዲሁም የአዲስ ኪዳንና የክርስቲያናዊ መዝሙራትን ትርጉሞች አዘጋጁ።

ሰሜን ሮዴሽያ ውስጥ የሚሰዮን ጣቢያዎች የመሠረቱት ሌሎች ሚስዮናውያን፥ የፓሪስ ወንጌላዊ ሚስዮናውያን ማኅበር፥ የሆላንድ ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን፥ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች፥ ባፕቲስቶች፥ በክርስቶስ ወንድማማች፥ እና የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። ስለ ሮዴሽያ የተመዘገበው ነገር የሚያመለክተው አስደናቂ ማስረጃ፥ ክርስቲያናዊ ወኪሎች ከ1914 ዓ.ም. በፊት በነበሩት የክፍለ ዘመኑ ሩብ ዓመታት ወደ አፍሪካ ዘልቀው የገቡበትን ኃይልና ፍጥነት ነው። እስከ አሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጨረሻ ሩብ ዓመታት ድረስ በክልሉ የማያቋርጥ ሥራ የነበረው፥ የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር ነበር። ከ1870 ዓ.ም. ጀምሮ ግን ወደ ስፍራው የሚገቡ የሮም ካቶሊኮችን ጨምሮ በዋናነት የፕሮቴስታንቶች ማኅበራት ቁጥር እየጨመረ ሄደ። በዚህም ሳቢያ፥ ቋንቋዎች ለጽሑፍ በሚያመች ሁኔታ ተስተካከሉ፥ የክርስትና ሥነ ጽሑፍ ዝግጅት ተጀመረ፥ የአውሮፓ ዘመናዊ መድኃኒት መጣ፥ ትምህርት ቤቶች በእጥፍ በዙ፥ የአብያተ ክርስቲያን ቁጥር ጨመረ። በ1914 ዓ.ም. ክርስትና በፍጥነት ያድግ ነበር። ጥቂት ቆይቶ በ1920 ዓ.ም. ደቡባዊ ሮዴሽያ ውስጥ 59,000 ፕሮቴስታንቶችና ወደ 28,000 የሚደርሱ የሮም ካቶሊኮች ነበሩ። የ1921 ዓ.ም. ቆጠራ እንደሚያመለክተው ደግሞ፥ ሰሜናዊ ሮዴሽያ ውስጥ 65,531 ፕሮቴስታንቶችና 76,084 የሮም ካቶሊኮች ነበሩ።

ኒያሳላንድ (ማላዊ)

ኒያሳላንድ ካርታ ላይ የምትሸፍነው ክልል አነስተኛ ቢሆንም፥ የሕዝቧ ብዛት ግን ከፍተኛ ነው። የዚህ ምክንያቱ የምድሪቱ ከፍታ ስፍራዎች በጣም ለምና ለጤና ተስማሚ መሆን ነበር።

ቀደም ባለው ምዕራፍ እንዳመለከትነው በኒያሳላንድ ሥራ የጀመረው የመጀመሪያ ሚስዮን የዩኒቨርስቲዎች ሚስዮናዊ ተልእኮ ለማዕከላዊ አፍሪካ ነበር። የዚህ ሚስዮን ሥራ መሳካት ቀዳሚ ምክንያት በከፊል ዊሊየም ፒ. ጃንሰን የተባለው ሚስዮናዊ ያከናወነው ተግባር ነው። ጠበቃ የነበረው አባቱ ገና የሦስት ዓመት ልጅ ሳለ ስለሞተበት ጃንሰንን ያሳደገችው እናቱ ነበረች። አክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ሳለ በትምህርትና በስፖርታዊ እንቅስቃሴው መልካም ውጤት ያለው ነበር። ከዚያ ለእንድያን ሲቭል ሰርቪስ ለመሄድ ተዘጋጅቶ ነበር። አክስፎርድ ውስጥ በነበረ ጊዜ ነው የዩኒቨርስቲዎች ሚስዮንን ጥሪ የሰማው። ከአምሳ ዓመት በላይ በሚስዮናዊነት ሠርቷል፥ ሰብኳል፥ ትምህርት ቤቶች መሥርቷል።



መጽሐፍ ቅዱስንና የጳሎት መጽሐፍ ከኒያሳላንድ ቋንቋዎች ወደ አንዱ ተርጉሚል። እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከፊሉንና አንዳንዶቹንም በሌሎች ሦስት ቋንቋዎች ተርጉሚል።

የዩኒቨርስቲዎች ሚስዮን እጅግ ብዙ ትምህርት ቤቶች፥ የሕክምና አገልግሎት መስጫዎችና የመምህራን ማሰልጠኛዎችን ያቋቋመው ብዙም ሳይዘገይ ነበር። አፍሪካውያን መጋቢዎችን የሚያሰለጥንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤትም ነበረው።

በኒያሳላንድ ከሠሩ ቀደምት ሚስዮኖች መካከል ሌላው፥ የሊቭንግስቶንያ ሚስዮን የተባለው ነበር። በቀደምት ሚስዮናውያን ከፍተኛ ጥረት በ1914 ዓ.ም. 10,000 አባላት ያሏት እስከመሆን የደረሰች ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ተችሏል።

ሌሎች የፕሮቴስታንት ሚስዮኖች ኒያሳላንድ ውስጥ ሥራቸውን የጀመሩት የስኮትላንድ ቤተ ክርስቲያን፥ የአውስትራሊያ ባፕቲስቶች፥ የደቡብ አፍሪካ አጠቃላይ ሚስዮን፥ እና የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስቶች ናቸው።

የሮም ካቶሊኮች እስከ 1901 ዓ.ም. ድረስ ቋሚ የሚስዮን ጣቢያ ግዛቱ ውስጥ አልመሠረቱም። የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ጥቂት አማኞች ብቻ ነበሯት። ከ1914 ዓ.ም. በኋላ ግን በፍጥነት ታድግ ጀመር።

ጥያቄዎች

1. በሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የወንጌል መስፋፋትንና እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ሥራ አስቸጋሪ ያደረገውና በደቡብ ምዕራብ አፍሪካ የተፈጸመው ነገር ምን ነበር?

2. በቤቹዋናላንድ የሠራው ትልቁና ቀዳሚው የሚስዮን ማኅበር የትኛው ነበር? አፍሪካውያንን ለመርዳት ያደረጋቸውን ሙከራዎች ይጥቀሱ።

3. የደቡብ አፍሪካው ቁስ ማንገና ሞኮኔ በ1891 ዓ.ም. ምን አደረገ?

4. ፖርቱጋል የካቶሊክ አገር ሆና ሳለ፥ በ1914 ዓ.ም. ሞዛምቢክ ውስጥ የነበረችው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በጣም አነስተኛ የሆነችው ለምን ነበር?

5. ደቡባዊ ሮዴሽያ ውስጥ ሥራ የጀመረው የመጀመሪያ የፕሮቴስታንት ሚስዮን የትኛው ነበር? ወዲያው ትልቅ ቤተ ክርስቲያን የሆነውስ የትኛው ነው?

6. ሰሜናዊ ሮዴሽያ ውስጥ የመጀመሪያው ሚስዮን ጣቢያ የተመሠረተው በየትኛው የአገሪቱ ክፍል ነበር? መሥራቹ ሚስዮን የቱ ነው?

7. የዩኒቨርስቲዎች ሚስዮን በኒያሳላንድ ከ1878-1914 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የሠራውን ሥራ በአጭሩ ይናገሩ።

በአፍሪካ ፈጣን የቤተ ክርስቲያን እድገት የታየበት ክፍለ ጊዜ ከ1878-1914 ዓ.ም.

የጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ (ታንዛኒያ)

ወንጌልን ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ያመጡት፥ የመጀመሪያዎቹ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ክራፍና ሬብማን የተባሉ መሆናቸውን ምዕራፍ 20 ውስጥ ተመልክተናል። እነዚህ ሚስዮናውያን፥ በጉጂቸው ሰሜን ታንዛኒያን የጎበኙ ቢሆንም፥ የሮም ካቶሊኮች በ1860 ዓ.ም. ወደ ስፍራው እስከመጡ ድረስ አሁን ታንዛኒያ ብለን በምንጠራው ስፍራ ቋሚ የሚስዮን ጣቢያ አልተቋቋመም ነበር። በ1870ዎቹ የመጨረሻ ዓመታት፥ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር እና የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር ሰሜን ምዕራብና ምዕራብ ታንዛኒያ ውስጥ የሚስዮን ጣቢያዎችን መሠረቱ። የዩኒቨርስቲዎች ሚስዮን አባላትም ደቡብ ታንዛኒያ ማላዊ ሐይቅ አካባቢ ባሉ ሦስት የሚስዮን ጣቢያዎች ውስጥ ይሠሩ ነበር።

ጀርመን ይህን ስፍራ የጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ ብላ በግልጥ የሰየመችው በ1885 ዓ.ም. ነው። ጀርመን ውስጥ የነበሩ ፕሮቴስታንቶች በሥፍራው ያላቸውን ፍላጎት እንዳሳዩ፥ ወዲያውኑ ብዙ የጀርመን ፕሮቴስታንቶች ክርስቲያናዊ ሥራ ለመጀመር ሚስዮናውያንን ወደ ስፍራው ለመላክ ተዘጋጁ። ጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ለመሥራት አዲስ የሚስዮን ማኅበር በርሊን ውስጥ የተቋቋመው በ1886 ዓ.ም. ነበር። ይህ ሚስዮን ‘‘በርሊን 3’’ በመባል እንዲታወቅ ተደረገ። ሚስዮኑ የመጀመሪያ ጣቢያውን ዳሬሰላም ውስጥ የከፈተው በ1887 ዓ.ም. ሲሆን፥ ከዚያም በታንጋ እና በዙሪያው ሌሎች ጣቢያዎችን ከፈተ።

ለብዙ ዓመታት ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የሠራው የበርሊን ሚስዮናውያን ማኅበር በ1891 ዓ.ም. ጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ሥራውን ጀመረ። እነዚህ ሚስዮኖች የመጀመሪያ ጣቢያዎቻቸውን የከፈቱት በስተደቡብ ከሚገኘው የማላዊ ሐይቅ አጠገብ ነው። እስከ 1914 ዓ.ም. ጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ በአጠቃላይ 22 ጣቢያዎች፥ 57 ሚስዮናውያንና 2,308 አባላት ነበሩ።

የሞሬቪያን ሚስዮን ጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ሥራውን የጀመረው በ1891 ዓ.ም. ነው። የዚህ ሚስዮን አባላት በደቡብ በኩል ማላዊ ሐይቅ አጠገብም ይሠሩ ነበር። በ1898 ዓ.ም. ደግሞ ከቪክቶሪያ ሐይቅ በስተደቡብ የሚገኘውን የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር ጣቢያ ተረከቡ። ሞሬቪያኖች በ1914 ዓ.ም. 15 ጣቢያዎች፥ 28 ሚስዮናውያንና 1,780 የተጠመቁ አባላት ነበሯቸው።

የላይፕዚግ ሚስዮናውያን ማኅበር በሰሜን በኩል ኪሊማንጃሮ ተራራ አካባቢ ሥራ ጀመረ። በአካባቢው የክርስትና ምሥክርነት የተጀመረው በቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አማካይነት ነበር። ከ1885 ዓ.ም. በኋላ ግን የእንግሊዙ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ሚስዮናውያን ከጀርመን ቅኝ ገዢዎች ድጋፍ አላገኙም። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ጣቢያዎቹን ለላይፕዚግ ማኅበር በመስጠት በ1893 ዓ.ም. በኬንያ በኩል ወዳለውና ኪሊማንጃሮ ልዩ ስሙ ታቬታ ወደተባለ ስፍራ ሄዱ። የላይፕዚግ ማኅበር በበኩሉ ሚስዮናውያኑ ይሠሩበት የነበረውን በኡካምባኒ አተባለው ስፍራ የነበሩትን ሁለት ጣቢያዎች ትቶ ሞሺ ወደተባለው አካባቢ በመዛወር የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ሥራን ተረከበ።


የታንዛኒያን የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሚስተር ሐርልበርትና ሚስተር ስታውፋከር የተባሉ ሰዎች ከቪክቶሪያ ሐይቅ በስተደቡብ የነበረውን ክልል እስከነበኙበት እስከ 1909 ዓ.ም. ድረስ ወደኋላ ተመልሰን ልንመለከት እንችላለን። የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን አባላት ወደ ጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ የገቡት በቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ጥያቄ ነበር። ይህ የሆነው በሚቀጥለው አኳኋን ነው። የዩጋንዳ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ሰው የነበሩት ጳጳስ ተከር እና ሚስተር ሐርልበርት ብዙ የጋራ ንግግሮችን አድርገው ነበር። በዚህ ንግግር ጳጳሱ ጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የነበራቸውን ሥራ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ለመውሰድ መዘጋጀት አለመዘጋጀቱን ይገልጡላቸው ዘንድ ሚስተር ሐርልበርትን ጠየቋቸው። የነበራቸው አንድ ጣቢያ ብቻ ሲሆን፥ ያም ቪክቶሪያ ሐይቅ ምሥራቃዊ ዳርቻ ናሳ እተባለው ስፍራ ላይ ነበር። ሌላው ሥራቸው ከነበረበት ከዩጋንዳ ይህን ሥራ መቆጣጠር ያስቸግር ነበር። ናሳ ታሪክ ያላት ስፍራ ናት። እዚያ የነበረው ሥራ የተጀመረው በ1888 ዓ.ም. ነበር። አሌክሳንደር ማኪ ከዩጋንዳ በተባረረ ጊዜ መጠለያ ያገኘው እዚያ ነው። ስለዚህ ሚስተር ሐርልበርትና ሚስተር ስታውፋከር አካባቢውን ከጎበኙ በኋላ፥ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን የናሳን ጣቢያ መውሰድ አለበት በማለት ወሰኑ። ከዚህ ሁኔታ ዘግየት ብሎ የመጀመሪያዎቹ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ሚስዮናውያን ናሳ ደረሱ።

ከ1878-1914 ዓ.ም. ባለው ጊዜ የሮም ካቶሊኮችም በንቃት ይሠሩ ነበር። ባጋሞዮ እተባለው ስፍራ ሥራ የጀመሩት መንፈስ ቅዱሳውያን አበው መሃል አገር ዘለቁ። ወዲያውኑ በርካታ ትምህርት ቤቶችና ማተሚያ ቤት አቋቋሙ። እስከ 1914 ዓ.ም. ሁለት ቪካርየት አፖስቶሊኮች፥ በ25 ጣቢያዎች የሚያገለግሉ 43 ካህናት፥ 29 ወንድሞች እያሉ የሚጠሯቸው የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና 50 እህቶች፥ ወደ 20,000 የሚደርሱ ክርስቲያኖች አፈሩ።

ሌሎች የሮም ካቶሊክ ድርጅቶችም ጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ መሥራት ጀመሩ። ቤነዲክትኖች በደቡብ የአገሪቱ ክፍሎች ይሠሩ ጀመር። በግዛቱ ምሥራቃዊ ክፍል የሚሠሩት ነጭ አበው ይባሉ የነበሩት ነበሩ። ወዲያውኑ አውሮፓውያን እህቶችና ሌሎች የሴቶች ማኅበራት የሮም ካቶሊካውያንን ሥራ በማስፋፋት ረገድ ከወንዶቹ ጋር ተባበሩ። እስካሁን ከተመለከትነው፥ ጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ እንግሊዞች ከያዙት ጋር ሲነጻጸር፥ የሮም ካቶሊኮች የክርስትና ትምህርት ከፕሮቴስታንቶች የተሻለ እድገት አሳይቷል።

ኬንያ

ስለ ኬንያ በመጨረሻ በተመለከትን ጊዜ፥ እዚያ የነበረው ብቸኛ ክርስቲያናዊ ሥራ፥ ባሕሩ ዳርቻ አካባቢ በፕሮቴስታንቶች የተከናወነው ብቻ መሆኑን አይተናል። በ1878 ዓ.ም. ደግሞ የተባበሩት የመቶዲስት ነጻ አብያተ ክርስቲያን እና የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር እዚያ የነበሩ ዋና ዋናዎቹ ሚስዮኖች ነበሩ። አብዛኛው የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አገልግሎት ያተኮረው፥ ነጻ በወጡና ፍሬሬታውን አካባቢ በነበሩ ባሪያዎች ላይ ነበር። በመቶዎች የሚቆጠሩ አፍሪካውያን ባሪያዎች ከዓረብ አሳዳሪዎቻቸው እየሸሹ ወደ ፍሬሬታውን ይሄዱ ጀመር። በመሆኑም ፍሬሬታውን ውስጥ የሚኖሩት ሌሎች አፍሪካውያን ክርስቲያኖች፥ ሸሽተው ለሚመጡ ባሪያዎች የሚያገለግሉ ማረፊያዎች መሥራት ጀመሩ። ባሪያ አሳዳሪ ከሆኑ ዓረቦች ዘንድ ሊመጣ የሚችል አመጽ እና የሸሹ ሰዎችን መከላከሉ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ ሚስዮናውያኑን ቢያስጨንቃቸውም፥ አፍሪካውያን ክርስቲያኖች ግን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሸሽተው የመጡ ባሪያዎችን ከመደበቅ አልተቆጠቡም። ዴቪድ ኮይ የተባለ አንድ የጊሪያማ ጎሳ አባል የሆነ ክርስቲያን፥ እነዚያን ሸሽተው የመጡ ሰዎች ፍሎዶዮ በተባለው ስፍራ ላይ ሊያስተምራቸው ተጋበዘ። በ1883 ዓ.ም. ዴቪድ ኮይ ወደ መንደሪቱ ዘልቆ በገባ የወንበዴዎች ቡድን ተሰዋና የመጀመሪያው ኬንያዊ ክርስቲያን ሰማዕት ሆነ። የመጀመሪያዎቹ የኬንያ ትምህርት ቤቶች የተፈጠሩት ፍሬሬታውን ውስጥ በቀድሞ ባሪያዎች ማኅበረሰብ ነው።



የመጀመሪያዎቹ አፍሪካውያን መምህራንና ወንጌላውያን በ1885 ዓ.ም. ካህናት የሆኑት ከነርሱው ነበር። በ1890 ዓ.ም. ወደ 2,000 የሚደርሱ የተጠመቁ እንግሊዛውያንና ጥቂት መቶዲስቶች ነበሩ። ይህ የመጀመሪያው በኬንያ የተደራጀና ቀጣይነት የነበረው የክርስትና ገጽታ ነው።

የስኮትላንድ ኢንዱስትሪያዊ ሚስዮን ከባሕር ዳርቻው ተነሥቶ ወደ መህል አገር በመዝለቅ ወንጌልን ወደ ኬንያ ውስጣዊ ክፍሎች ያደረሰው በ1891 ዓ.ም. ነው። የሚስዮኑ አባላት ዓላማ ማቻኮስ በተባለ ስፍራ የሚስዮን ጣቢያ መመሥረት ነበር። ነገር ግን የአፍሪካ ክርስቲያኖችና ሚስዮናውያን የመጀመሪያ ቡድን ክብዌሲ እተባለው ስፍራ ሲደርስ ቆመ።

ስኮትላንዳውያን እዚያ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረትና የሙያ ትምህርት ቤት ለማቋቋም አስበው ነበር። ከሰባት ዓመታት ቆይታ በኋላ ግን ስፍራው ያን የመሰለ የሚስዮን ጣቢያ ለመመሥረቻነት ትክክለኛ ቦታ አይደለም ብለው ወሰኑ። የሚስዮን ጣቢያው በ1898 ዓ.ም. ወደ ኩኩዩ ተዛወረ። ከዚያም የስኮትላንድ ቤተ ክርስቲያን ተረከበችው።

በ1887 ዓ.ም. የጀርመን ኒዩኪርቸነር ሚስዮን ላሙ በተባለ ስፍራ መሥራት ጀመረ። በኋላ ግን ታና ወንዝ ላይ ወደሚገኘውና እንጋኦ ወደተባለው ስፍራ ተንቀሳቀሰ። ምሥራቃዊ ኡካምባኒ ተመሳሳይ አካባቢ፥ የቤቫሪያ ወንጌላዊት ሉተራን ሚስዮን የተባለው ድርጅት ሥራ ጀመረ። ይህን ሚስዮን የላይፕዚግ ሚስዮን ተረከበውና፥ በበኩሉ ሁለት ጣቢያዎችን በ1914 ዓ.ም. ለአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ሰጠ።

ሚስዮናውያን በተሻለ ፍጥነት ወደ መሀል አገር እየገፉ መሄድ የጀመሩት ከ1890 ዓ.ም. በኋላ ነበር። በ1893 ዓ.ም. ስቱወርት ዋት የተባለና ራሱን የቻለ ሚስዮናዊ ከሚስቱና ከቤተሰቡ ጋር ከባሕሩ ዳርቻ ወደ ማዕከላዊ ኬንያ አመራ። ከዚያም ኡካምባኒ ውስጥ በምትገኘውና ንጌላኒ በተባለችው ቦታ ሠፈረ። የዋት ቤተሰቦች በጤንነት መታወክ ምክንያት ኬንያን እንዲለቁ በተገደዱ ጊዜ፥ የሚስዮን ጣቢያቸውን ለአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን አስረከቡ።

በ1894 ዓ.ም. የመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ክፍሎች ጊሪማ፥ ታኢታ፥ ኪካምባ፥ ኒይካ፥ ፎኮሞና አሮምኛ ወደተባሉ ቋንቋዎች ተተረጎሙ። በ1895 ዓ.ም. የወንጌል ምሥክርነት በኬንያ የባሕር ዳርቻ በሚገባ ተመሥርቶ ነበር። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ሚስዮናውያን ወደ መሀል አገር መግፋት ጀምረዋል። ያም ሆኖ የኬንያ መሀል አገር ሰፊ ክፍል የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መልካም የምሥራች አልደረሰውም። ያኔ ይፈለግ የነበረው፥ ራእይ ኖሮት ወንጌል ወዳልደረሰባቸው የመሀል አገሮች ሊገፋ የሚችል አዲስ ሚስዮን ነበር። ለዚህ ሥራ እግዚአብሔር ፒተር ካምረን ስካት የተባለውን ሰው ጠራው።

ፒተር ካምረን ስካት ግላስኮው አጠገብ መንገድ ዳር ባለና ዝቅተኛ ኑሮ ባለው አንድ ቤተሰብ ውስጥ መጋቢት 7 ቀን 1867 ዓ.ም. ተወለደ። ወላጆቹ ታማኝ ክርስቲያኖች ነበሩ። የስካት ቤተሰቦች በጎዳር ወር 1879 ዓ.ም. ወደ አሜሪካ ተሰደው ፊላደልፍያ አጠገብ ሰፈሩ። አሥራ ስድስት ዓመት ሲሞላው በጎትመት ሥራ ሠራተኛነት ተቀጥሮ ነበር። ብዙም ሳይቆይ በጤንነቱ ምክንያት ሥራውን ተወው። ስኮትላንድን ከጎበኘ በኋላ፥ ወደ አሜሪካ ኮሌጅ ገባ። በጎዳር ወር 1890 ዓ.ም. በምዕራብ አፍሪካ ሚስዮናዊ ለመሆን ከአሜሪካ ወጣ። ለተወሰነ ጊዜ ጆን ከተባለ ወንድሙ

ጋር ኮንጎ ውስጥ ሠርቶ ነበር። ብዙም ሳይቆይ ጆን ስካት በትኩሳት በሽታ ስለሞተና እርሱም በጠና ስለታመመ ወደ አሜሪካ ተመለሰ።

ፒተር ስካት ወደ አሜሪካ ከተመለሰ በኋላ የምሥራቅ አፍሪካን መሀል አገሮች በወንጌል በመድረስ ረገድ ስላለው የሚስዮናውያን አስፈላጊነት ለጓደኞቹ ነገራቸው። በነሐሴ ወር 1895 ዓ.ም. ሰባት አባሎች ያሉት አንድ ቡድን ለመሸኘትና ለመመረቅ በተደረገ ስብሰባ ላይ፥ ሌሎች አራት ወንዶችና ሦስት ሴቶች፥ ማርጋሬት የተባለችውን የፒተር እህት ጨምሮ ለዚህ አገልግሎት ወጡ ወይም ተለዩ። ኋላም ስኮትላንድ ላይ አንድ ሰው ተጨመረላቸው። ፒተር በሙሉ ድምጽ ተመረጠና የቡድኑ መሪ ሆነ። በሚቀጥለው ዕለት በመርከብ ከኒውዮርክ ተነሥተው ጥቅምት 17 ቀን ሞምባሳ ደረሱ። ጸሎትና ምክክር ከተደረገ በኋላ ሴቶቹን እዚያው ለመተው ተወሰነና ወንዶቹ ወደ መሀል አገር የሚያደርሰውን ጉዞ ተያያዙት። ታኅሣሥ 12 ቀን 1895 ዓ.ም. ቡድኑ ኒዛዊ እተባለው ስፍራ ደረሰ። ስካትና ጓደኞቹ የመጀመሪያውን የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ጣቢያና የመጀመሪያውን የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት የወሰኑት እዚያ ነበር። ሴቶቹ ወደ ሞምባሳ እንዲመጡ ተደረገ። እነዚህ የመጀመሪያ ሚስዮናውያን ከኒዛዊ በኋላ ሳካይና ኪሉንጉ በተባሉ ስፍራዎች የሚስዮን ጣቢያዎችን አቋቋሙ። ጥቅምት 3 ቀን 1896 ዓ.ም. ካንጉንዶ እተባለው ስፍራ ላይ ሌላ የሚስዮን ጣቢያ ተመሠረተ። ፒተር ስካት ታኅሳስ 4 ቀን 1896 ዓ.ም. እስከሞተ ድረስ፥ ኡካምባኒ ውስጥ የሠራው ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ነበር። ለእግዚአብሔር ጥሪ ታዛዥ በነበረው ሰው የተጀመረው ይህ ሥራ ለሌሎች ተላለፈ።

በ1903 ዓ.ም. የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ዋና መሥሪያ ቤቱን ከአዲሱ የባቡር መሥመር ውጭ ከሆነው ከካንጉንዶ ወደ ኪጃቢ አዛወረ። ከኪጃቢ በኋላ ሌሎች ብዙ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ጣቢያዎች ተከፍተዋል። ነገር ግን በዚህ አጭር ጥናቶችን ሁሉንም ለመጥቀስ አንችልም።

የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን በኬንያ መሀል ምድር የጀመረውን ሥራ ገፋበት። ከዚያ ወዲህ ሌሎቹ ሚስዮኖችም ይበልጥ ወደ ምዕራብ ይገፉ ጀመር። የስኮትላንድ ቤተ ክርስቲያን (ፕሬስቢቴሪያን) ሚስዮን በ1897 ዓ.ም. ናይሮቢ አጠገብ አዲስ ጣቢያ ሲከፈት፥ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበርም በ1901 ዓ.ም. እንዲሁ አደረገ። በ1902 ዓ.ም. የጓደኞሞች ኢንዱስትሪያዊ ሚስዮን ካይሞሲ በተባለ ስፍራ ሥራውን ጀመረ። በ1905 ዓ.ም. ደግሞ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ የተባለው ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ የሚስዮን ጣቢያውን ኪማ እተባለው ስፍራ ከፈተ። በ1906 ዓ.ም. የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ለጎሳ

አለቆች ልጆች የሚሆን ትምህርት ቤት በማሲኖ ሲቆረቁር፥ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስቶች ደግሞ ደቡብ ኒያሳ ውስጥ የመጀመሪያ ጣቢያቸውን ኪንዶ ባሕረ-ሰላጤ ላይ አቋቋሙ።

ቀደምት ሚስዮናውያን በሙሉ ነጮች አልነበሩም። ከእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ሚስዮናውያን መካከል ከደቡብ አፍሪካ ሻንጋን ከተባለ ነገድ የሆነ ዮሐና ምቢላ ይገኝበታል። ምቢላ ዘመናዊውን ማረሻ ያስተዋወቀ፥ እጅግ ታዋቂና ብርቱ ቀደምት የኪማ ወንጌላዊ ነበር። በሕይወቱ ባሳየው ምሳሌነት ወደ ጌታ ያመጣው የአገልግሎቱ ፍሬ፥ ዮሐና ኦዌንጋ የተባለ አማኝ ከአንድ የሚስዮናዊ ቡድን ጋር በ1914 ዓ.ም. ወደ ኮንጎ ተጓዘ። ኪማ ውስጥ ያለው ሥራ ከተጀመረ ገና ዘጠኝ ዓመት ሲሆነው ኦዌንጋና አያሌ ነጭ ሚስዮናውያን በ1915 ዓ.ም. ተጨማሪ ጉዞ በማድረግ ላይ ሳሉ ሞቱ። ታቪታ ከተባለው ስፍራ የተነሣው ሌላ አፍሪካዊ፥ ሻድራክ ምሊዋ ወደ ማዕከላዊ ኬንያ ተጉዞ፥ ኪሩጎያ አተባለው ስፍራ ከሠፈረው የመጀመሪያ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ሚስዮናውያን ቡድን ጋር ተገናኝቶ ነበር። ይህ ሰው ሕይወቱ እስካለፈችበት እስከ 1960ዎቹ ዓ.ም. የመጀመሪያ ዓመታት ድረስ እዚያው በመኖር እጅግ ትልቅና ፍሬያማ የሆነች የኩኩዩዎች ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው መሥርቷል። ከመጀመሪያዎቹ አፍሪካውያን ክርስቲያኖች ብዙዎቹ ታላላቅ መንፈሳውያን ነበሩ። የማሳይ ክርስቲያንና የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረው ሞሎንኬት ኦሊ ሲምፕሊ የተባለ ሰው ወደ አሜሪካ ሄደ። መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በመግባት ስለ እግዚአብሔር ቃል ይበልጥ ለማወቅ ሲል በ1909 ዓ.ም. ከብቶቹን ሁሉ ሸጧል።

ከ1910 ዓ.ም. በኋላ የወንጌል መልእክት በኬንያ ብዙ አዳዲስ ስፍራዎች የተስፋፋ ሲሆን፥ አንዳንድ አዳዲስ ሚስዮኖችም ወደ አገሪቱ ገብተዋል። ለምሳሌ በ1911 ዓ.ም. የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ቪክቶሪያ ሐይቅ አጠገብ የኒያካችን ጣቢያ ከፈተ። በ1912 ዓ.ም. በኬንያ የመጀመሪያው የመቶዲስት አገልጋይ የነበረውና የፖኮሞ ጎሳ አባል የሆነው ቁስ ጆሴፍ ጃራ ከሞምባሳ ወደ ሜሩ በእግር በመጓዝ የመጀመሪያውን የመቶዲስት ሚስዮን ጣቢያ በአካባቢው መሠረተ። በዚሁ ዓመተ ምሕረት ጳንጠቆስጣዊ የእግዚአብሔር ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን የተባለ ሚስዮን የመጀመሪያ ጣቢያውን ኒያንጎሪ እተባለ ስፍራ ላይ ከፈተ።

በ1914 ዓ.ም. ጆሃና አዋሎ የተባለ ሰው የኖሚያ ሉአ ሚስዮንን ምዕራብ ኬንያ ውስጥ ባቋቋመ ጊዜ፥ የመጀመሪያው ነጻ ወይም ተገንጣይ ቤተ ክርስቲያን ኬንያ ውስጥ ተመሠረተ። የኖሚያ ሉአ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ኬንያ ውስጥ የለችም።

የመጀመሪያው ዘመናዊ ቋሚ የኬንያ ካቶሊካዊ ሚስዮን ጣቢያ የተቋቋመው፥ በ1890 ዓ.ም. ሞምባሳ ውስጥ የመንፈስ ቅዱሳውያን አበው በተባለው ቡድን ነበር። የመንፈስ ቅዱሳውያን አበው አባላት በ1891 ዓ.ም. ቮይ አጠገብ ቡራ በተባለ ስፍራ የሚስዮን ጣቢያ የከፈቱ ሲሆን፥ በ1899 ዓ.ም. ከናይሮቢ በስተምዕራብ ሊሙሩ አተባለ ስፍራ ደርሰው ነበር። የኡካምባ አገር የታሰሰው በ1907 ዓ.ም. ሆኖ፥ የካባ የሚስዮን ጣቢያና የማቻኮስ ወረዳ ትምህርት ቤት ሥራ የተጀመረው ደግሞ በ1913 ዓ.ም. ነበር። የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በተጀመረበት በ1914 ዓ.ም. የመንፈስ ቅዱሳውያን አበው ሚስዮኖች ኡካምባኒ በተባለው ስፍራ በኩኩዮዎች መካከል፥ ቡራ፥ ምዋንዳ፥ ታይታ በተባለ ስፍራና በባሕር ዳርቻው በብዙ ስፍራዎች ነበሩ።

ዩጋንዳ

ክርስትና ወደ ዩጋንዳ የመጣው፥ ዳሊንግተን ሙፍታና ሄንሪ ስታንሊ በተባሉ ሰዎች አማካይነት እንደነበረ ተመልክተናል። የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አባላት፥ ንጉሥ ሙቲሳ ዋና ከተማ ውስጥ በ1877 ዓ.ም. የሚስዮን ጣቢያ አቋቋሙ። የካቶሊክ ሚስዮን በ1879 ዓ.ም. ንጉሥ ሙቲሳ ግቢ ደረሰና ሥራ ለመጀመር ፍቃድ ጠየቀ። የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አባል አሌክሳንደር ማኪ ካቶሊኮች ምንም ዓይነት ክርስቲያናዊ ሥራ ወደሌለባቸው ስፍራዎች ሄደው ሥራ እንዲጀምሩ አሳሰባቸው። እነርሱ ግን አሳቡን ሳይቀበሉት ቀሩ። ንጉሥ ሙቲሳም እዚያ እንዲሰፍሩ ለካቶሊኮቹ ፈቀደላቸው። ብዙም ሳይቆይ ንጉሥ ሙቲሳና የቡጋንዳ ሕዝቦች በሁለቱ የእምነት ክፍሎች ትምህርቶች ግራ ተጋቡ። የካቶሊኮች ወደ ስፍራው መምጣት የወንጌል መልእክት እንዲሰፋፋ ከመርዳት ይልቅ፥ ግራ መጋባትና ጥላቻን በመፍጠር እንቅፋት ሆነ። ንጉሡና አለቆቹ በታኅሣሥ ወር 1879 ዓ.ም. ሁለቱንም የክርስትናና የእስልምና እምነቶች በግልጥ በመካድ ለአባቶቻቸው እምነት ታማኞች እንዲሆኑ አውጀው ሚስዮናውያኑ ሕዝቡን እንዳያስተምሩና ሕዝቡም ሚስዮናውያኑን እንዳይነበጉ አዘዙ። የዓረብ ነጋዴዎች ወደ አገሪቱ በብዛት በመግባትና በመታወቅ ላይ ነበሩና ንጉሥ ሙቲሳ በሐምሌ ወር 1880 ዓ.ም. ሙስሊም መሆኑን በአዋጅ አሳወቀ። ያም ሆኖ በጣም አመዛዛኝ መሪ ለመሆንና የዓረብ ሐሰተኛ ወሬዎች እንዳያታልሉት በማሰብ፥ ሕዝቡ የማኪይን የኢንዱስትሪ (የሙያ ትምህርት) ሥልጠና መከታተል እንዲችሉ ነጻነት ሰጣቸው። ለማኪይ የነበረው አክብሮት ታላቅ ነበር።

ሚስዮናውያኑ እንዲያስተምሩና እንዲሰብኩ በ1880 ዓ.ም. እንደገና ሲፈቀድላቸው ተልዕኳቸውን ለመፈጸም ሙከራ ጀመሩ። መጋቢት 18 ቀን 1882 ዓ.ም. በተካሄደው በመጀመሪያው የእንግሊዝ ሚስዮን የጥምቀት ሥነ-ሥርዓት አምስት ወጣቶች ተጠመቁ። በዚያን ዕለትና በጎዳር 1884 ዓ.ም. መካከል 88 ሰዎች ይህን ሥርዓት ፈጽመዋል። የሮም ካቶሊኮች ወደ እምነታቸው ያመጡት ሰው ብዛት ከዚህ እንደሚልቅ ይናገራሉ። ይህ ነገር ለዓረቦች ጥላቻ ይበልጥ ስላጋለጣቸው ከጥቅምት 1882 ዓ.ም. እስከ ሐምሌ 1885 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ስፍራቸውን ትተው ከሐይቁ በስተደቡብ ወዳለው ስፍራ ሄዱ።

የካንተርበሪው ሊቀጳጳስ በ1884 ዓ.ም. ጀምስ ሃኒንግቶንን ማዕከሉ ቡጋንዳ ውስጥ ለሆነው "የምሥራቃዊ ኢኳቶሪያል አፍሪካ" አውራጃ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ አድርጎ ሾመው። እርሱም በጥር ወር በ1885 ዓ.ም. ሞምባሳ ደረሰና የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አባላት እንዳደረጉት በታንጋኒካ በኩል ከመሄድ ይልቅ፥ በኬንያ በሚያቋርጠው ቀጥተኛ መንገድ ወደ ቡጋንዳ ሄደ። ጳጳሱ ሃንኒግቶን ከምሥራቅ በኩል ወደ ቡጋንዳ ድንበር በቀረበ ጊዜ፥ ያኔ የነበረው አዲስ ንጉሥ ምዋንጋ ፍርሃት አደረበትና አስገደለው። ዘግየት ብሎም ቡጋንዳ ውስጥ በነበሩት ክርስቲያኖች ላይ ስደት አስነሣ። በዚሁ መሠረት ንጉሡ ሴሩዋንግ፥ ካኩምባና ሉጋላማአ የተባሉ ሦስት የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አባላትን ሰውነታቸው በስለት ተቆራርጦ ወደ እሳት እንዲጣሉ በማድረግ አስገደላቸው። ስለዚህ ጥር 30 ቀን 1885 ዓ.ም. የተገደሉ እነዚህ ሦስት ሰዎች የመጀመሪያዎቹ የዩጋንዳ ክርስቲያን ሰማዕታት ሆኑ።

ንጉሥ ምዋንጋ በግንቦትና በሰኔ ወራት 1886 ዓ.ም. በአገዛዙ ውስጥ አሰቃቂ የተባለውን ስደት አዘዘ። የፕሮቴስታንትም ሆኑ የሮም ካቶሊክ ክርስቲያኖች እየተያዙ በእሳት እንዲቃጠሉ ተደረገ። ማኪይ ይህን ስደት በሚቀጥሉት ቃሎች ገልጠታል፦ "በመጀመሪያ በዋና ከተማይቱ የሚገኙ ክርስቲያኖች ተያዙ። 12 ያህል ሰዎች በአንድ ጊዜ ታረዱ...ብዙዎቹ በጦር እየተወጉ ተገደሉ። ሌሎቹም በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ተገደሉ። ሠላሳ ሁለት ሰዎች በአንድ ትልቅ የእሳት ነበልባል ከነሕይወታቸው ተቃጠሉ።" በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው እምነት ምክንያት ሕይወታቸውን የሰጡት እነዚህ ሰዎች "የዩጋንዳ ሰማዕታት" በመባል ይታወቃሉ።

ማኪይ፥ ንጉሥ ምዋንጋ ሊገድለው ስለፈለገ፥ በሐምሌ ወር 1887 ዓ.ም. ቡጋንዳን ለቆ መሄድ ግድ ሆነበት። ሰሜን ታንጋኒካ ውስጥ ናሳ እተባለ ስፍራ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበርን ጣቢያ ካቋቋመ በኋላ በ1890 ዓ.ም. በትኩሳት ሕመም ሞተ።

ከ1887-1890 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ በቡጋንዳ ታላላቅ የፖለቲካ ለውጦች ተደረጉ። ንጉሥ ምዋንጋና ወንድሞቹ መንግሥቱን ለመቆጣጠር እርስ በርሳቸው ውጊያ ገጠሙ። ወንድማማቾቹ እያንዳንዳቸው በተለያዩ ቡድኖች ይደገፉ ነበር። ሙስሊሞች አንዱን ወገን፥ ፕሮቴስታንቶችና ካቶሊኮች ደግሞ ሌላውን ደገፉ። ይህ ሲሆን ሳለ ካፒቴን ሉጋርድ በሚባል አዛዥ የሚመራ የእንግሊዝ ንጉሣዊ አገዛዝ የምሥራቅ አፍሪካ ኩባንያ ቡጋንዳ ደረሰና ትኩረት የሳበ አዲስ ኃይል ሆነ። በመጨረሻም በ1894 ዓ.ም. ሰኔ ወር ታላቁ የእንግሊዝ መንግሥት ዩጋንዳን በሞግዚትነት የሚያስተዳድራት መሆኑን ግልጥ አደረገ። ይህም የፖለቲካው ውጊያ በሰላም እንዲያበቃና የወንጌል ሥራም እንዲቀጥል የሚያስችል ሁኔታ ፈጠረ።

በዚህ ጊዜ የፕሮቴስታንት ሚስዮን በፖለቲካው ግንባር ጸጥ ቢልም፥ በመጋቢት ወር 1896 ዓ.ም. 6,905 የተጠመቁ ክርስቲያኖች እንደነበሩት፥ ከእነዚህ ውስጥ 1,335ቱ የቅዱስ ቊርባን ተካፋይ አባላት እንደሆኑ፥ የመሠረተ እምነት ትምህርት የሚከታተሉት ደግሞ 2,591 መሆናቸውን፥ እንዲሁም ‘‘አንባቢ ሠራዊት’’ [Army of Readers] የሚባሉ (ለመጠመቅም ሆነ ከመሃይምነት ለመላቀቅ የሚፈልጉትን ጨምሮ) 57,380 ሰዎች እንደነበሩት አሳወቀ።

የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር የታማኝነት ሥራዎች ውጤቱ የዩጋንዳ ቤተ ክርስቲያን መመሥረቷ ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመነሻው አንስቶ እራሷን የምትደግፍና ወንጌልን የምታወጅ ነበረች። የቡጋንዳ አብያተ ክርስቲያን በአብዛኛው እራሳቸውን የሚያስተዳድሩና የሚደግፉ፥ የራሳቸውን አደረጃጀት ያበጁ፥ የአገሪቱ ተወላጅ ሠራተኞችን ደሞዝ የሚከፍሉ ነበሩ። የበላይ አካሉ ሲኖድ የሆነ የምዕመናን ጉባኤ አደረጃጀት ከፍተኛውን ድርሻ አፍሪካውያን ወስደው መደራጀት ጀመረ። ቡጋንዳዎች ሚስዮናዊ ተግባራትን በታላቅ ትጋት የሚፈጽሙ መሆናቸውን አረጋገጡ። ድርጅታቸው ከአንድ ጊዜ በላይ እምነቱን ለጎረቤት ነገዶች አስታውቋል። የክርስቲያንን መልእክት ለሌሎች በማስፋፋቱ ረገድ አውሮፓውያኑ ተባበሯቸው። በዚሁ መሠረት ወደ ክርስትና በቡድን የሚለወጡ ሰዎችን ማየት ተጀመረ። ከአንድ ትውልድ ዕድሜ ባነሰ ጊዜ ውስጥ የፕሮቴስታንት ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አማካይነት በሚያስደንቅ ፍጥነት አደጉ። የተጠመቁ ሰዎች ቁጥር በ1914 ዓ.ም. 98,447 ደርሶ ነበር።

ከ1894 ዓ.ም. በኋላ የሮም ካቶሊክ ሚስዮን በፍጥነት አደገ። የነጭ አበው የተባለው ማኅበር ከእንግሊዝ ከመጣውና የሚል ሂል አበው ከተባለው ጋር በመተባበር ብዙ የሚስዮን ጣቢያዎችን ዩጋንዳ ውስጥ

አቋቋሙ። እንደ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር እነርሱም ትምህርት ቤቶችን ከፍተዋል። ቢሆንም በ1914 ዓ.ም. የነበሯቸው ተማሪዎች የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበርን እንድ ሦስተኛ ብቻ ነበሩ። ካቶሊኮች በ1914 ዓ.ም. ወደነርሱ እምነት የተለወጡና ከ135,000 የሚበልጡ ሰዎች ዩጋንዳ ውስጥ እንዳሏቸው ይናገሩ ነበር። ዩጋንዳ በ1914 ዓ.ም. አፍሪካ ውስጥ ጠንካራና ትልቅ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የሚገኝባት ቀደምት አገር ነበረች።

ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ከ1878-1914 ዓ.ም. ለወንጌል መልእክት አስቸጋሪ አገር ሆና ቆይታለች። ከ1878 ዓ.ም. በፊት የነበረው የሮም ካቶሊክ ሚስዮን ሥራውን እዚያ ቢጀምርም፥ ወደ እምነቱ የተለወጡት ሰዎች ቁጥር ጥቂት ነበር።

ከሮማውያን ሚስዮን ውጭ የነበሩና በ1880ዎቹ አቢሲኒያ ውስጥ ለመሥራት የሞከሩ ሁለት ሚስዮኖች ምንም ውጤት አላገኙም። ከ1881-2 ዓ.ም. ወደ ኦሮሞዎች መጥቶ የነበረው የስዊድን ሚስዮን በሱዳን በኩል ወደ አገሪቱ ለመግባት ሞክሮ ነበር። የሚስዮኑ አባላት በአባይ ወንዝ መሥመር ከካርቱም 576 ኪሎ ሜትር ፋማካ ወደተባለውና በሱዳንና በአቢሲኒያ ድንበር ላይ ወዳለው ስፍራ ለመድረስ ቢችሉም፥ አገሪቱ በጣም የተናጋች ሆና ስላገኟት ወደ ካርቱም ተመለሱ። ቆይቶ ደግሞ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ሚስዮን ኢትዮጵያ ውስጥ ለመሥራት ሞከረና ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ለመስማማት ሳይችል ቀረ።

በ1914 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ውስጥ የበላይነቱን ስፍራ የያዘችው የኮፕቲክ (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ) ቤተ ክርስቲያን ናት። የፕሮቴስታንትና የሮም ካቶሊካዊት አብያተ ክርስቲያን በምድሪቱ ላይ የሚያከናውኑት የወንጌል ሥራ ገና ደካማ ነበር።

ሱዳን

ደቡብ ማዕከላዊ ሱዳን ውስጥ የካቶሊክ ሚስዮን የተከፈተው በ1873 ዓ.ም. ዳንኤል ኮምቦኒ በተባለ ሰው አማካይነት ነበር። በ1883 ዓ.ም. ግን መሐመድ አሕመድ የተባለ ሰው የሙስሊሞች መሢሕ ነኝ ብሎ ሱዳን ውስጥ በመነሣት፥ በማንኛውም የውጭ ዜጋ ላይ አመፅ አስነሥቶ ይመራ ጀመር። በዚሁ መሠረት የካቶሊክ ሚስዮናውያን በማህዲ (በመሐመድ አሕመድ) ተያዙና ሦስቱ እሥር ቤት እንዳሉ ሞቱ። ከ1883-1896 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ማህዲ ሱዳንን ከሌላ እምነት

በመከላከል ተከታዮቹ በሙሉ በጥብቅ የእስልምና ሕጎች እንዲኖሩ አዘዘ። በ1896 ዓ.ም. የግብፅና የእንግሊዝ ጦር ማህዲን ድል አደረገና የቅኝ ግዛት መንግሥት ካርቱም ውስጥ ተመሠረተ።

አዲሱ የቅኝ ገዢ መንግሥት ሙስሊሞችን እንዳያስቆጣ በመጠንቀቅ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ሰሜን ሱዳን ውስጥ ካሉት ዓረቦች መሀል እንዳይሠሩ ከለከለ። በአገሪቱ ደቡብ ክፍል ግን ከአፍሪካውያን ጋር ለመሥራት ነጻ ነበሩ። በ1900 ዓ.ም. የአሜሪካ ፕሬስቢቴሪያኖች ሱዳን ውስጥ ሥራ ጀመሩ። በ1906 የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አባላት በዩጋንዳ ወሰን በኩል ደቡብ ሱዳን ገቡ። የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር በ1914 ዓ.ም. አምስት የሚስዮን ጣቢያዎች ደቡብ ሱዳን ውስጥ ነበሩት።

ጥያቄዎች

1. ጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ሦስት የጀርመን የሚስዮን ማኅበሮችን በመጥቀስ፥ የሠሩባቸውን አጠቃላይ የሀገሪቱን ክፍሎች ይግለጡ።

2. የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ታንጋኒካ ውስጥ ሥራ የጀመረው መቼ ነበር? እንዴት ነው ይህ የሆነው?

3. የመጀመሪያው ኬንያዊ የክርስቲያን ሰማዕት ማነው? የተገደለው በማንና ለምን ነበር?

4. የፒተር ካምረን ስካትን ቀዳሚ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ ይግለጡ።

5. ‘‘የዩጋንዳ ሰማዕታት’’ እነማን ነበሩ? ለምንድነው የተገደሉት?

6. የዩጋንዳን ቤተ ክርስቲያን እድገት ባጭሩ ያስረዱ።

7. የሚስዮናውያን ሥራዎች በኢትዮጵያ እጅግ በዝግታ ያደጉበት ምክንያት ምን ነበር?

8. ፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ሥራ የጀመሩት በየትኛው የሱዳን ክፍል ነው?